ጅማ ዩኒቨርሲቲ

የሶሻል የ ሣይንስና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሁፍ ( አማርኛ) ትምህርት ክፍል ድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

" የጽህፈት ክሂል ማስተማሪያ ዘዴና የተማሪዎች ድርሰት የመፃፍ ብልሃት ተዛምዶ በገነት አቦ አጠቃላይ ሁለተኛና መሠናዶ ትምህርት ቤት በ11ኛ ክፍል ተተኳሪነት"

በ

ሞገስ አማረ

ነሀሴ 2013 ዓ.ም

ጅማ ዩኒቨርስቲ

ጅማ ዩኒቨር

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ሶሻል ሣይንስና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ፅሁፍ ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

"የፅህፈት ክሂል ማስተማሪያ ዘዴና የተማሪዎች ድርሰት የመፃፍ ብልሃት ተዛምዶ" በገነት አቦ አጠቃላይ ሁለተኛና መሠናዶ ትምህርት ቤት በ11ኛ ክፍል ተተኳሪነት

በ

ሞገስ አማረ

ዋና አማካሪ፡-ለማ ንጋቱ (ዶ/ር)

ረዳት አማካሪ፡-ሙሀመድ ጀማል

ነሀሴ 2013 ዓ.ም

**ጅማ ዩኒቨርሲቲ**

**የሶሻል ሣይንስና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ**

**የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ፅሁፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር**

**በገነት አቦ 2ኛና መሠናዶ ት/ቤት የፅህፈት ክሂል ማስተማሪያ ዘዴና የተማሪዎች ድርሰት የመፃፍ ብልሃት ተዛምዶ በ 11ኛ ክፍል ተተኳሪነት**

**በ**

**ሞገስ አማረ**

**የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ**

**ስም**

--------------------------------------------- ---------------------

**አማካሪ**

--------------------------------------------- -----------------------

**ፈታኝ**

--------------------------------------------- ------------------------

# ማረጋገጫ

የሰውን ስራ፣ሀሣብና መረጃ ተገቢ የሆነ ምንጭ ሣይጠቅሱ የራስ አስመስሎ ማቅረብ ሙያዊ ታማኝነትን የሚያሣጣ መሆኑን በሚገባ አውቃለሁ፡፡ስለሆነም ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ የራሴ መሆኑንና በተዛማጅነት የተጠቀምኩባቸውን ፅሁፎች ሁሉ ምንጫቸውን በመጥቀስ በትክክል በዋቢነት ያቀረብኩ መሆኔን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

**ሞገስ አማረ ደርሶ**

## ምስጋና

በቅድሚያ ጥናቱን አስጀምሮ ላስጨረሰኝ ለልዑል እግዚያብሔር ክብርና ምስጋና ይድረሰው፡፡በመቀጠል ጥናቱ እንዲሣካ ውድ ጊዚያቸውን መስዋዕት አድርገው በየጊዜው ሳይሰለቹ ስህተቶችን በማረም፣የአሰራር ስልቶችን በመጠቆምና በመደገፍ ክትትላቸው ላልተለየኝ አማካሪዎቼ ለዶ/ር ለማ ንጋቱና ለአቶ ሙሀመድ ጀማል ምስጋናዬ እጅግ የላቀ ነው፡፡እንዲሁም በዩኒቨርሲቲው በነበረኝ ቆይታ በሞራልም ሆነ በሀሣብ እገዛው ላልተለየችኝ ለውድ ባለቤቴ ለወ/ሮ ያለምወርቅ በለጠ ያለኝን ልባዊ ምስጋና ለመግለፅ እወዳለሁ፡፡

በመጨረሻም የመመረቂያ ፅሁፉን ለማከናወን የሚያስፈልገኝን በጀት በመመደብ እገዛ ላደረገልኝ ለጅማ ዩኒቨርሲቲ ፣እንዲሁም በጥናቱ ሂደት አስፈላጊውን መረጃ በመስጠት ለተባበሩኝ ለገነት አቦ 2ኛና መሰናዶ ት/ቤት የአማርኛ ቋንቋ መምህራንና የት/ቤቱ አስተዳደር ሠራተኞችና ለስራው መሳካት የበኩላቸውን አስተዋፅኦ ላበረከቱልኝ ግለሰቦች በሙሉ ምስጋናዬ የላቀ ነው፡፡

# አጠቃሎ

ይህ ጥናት ዋና አላማ አድርጎ የተነሳው የፅህፈት ክሂል ማስተማሪያ ዘዴና የተማሪዎች ድርሰት የመፃፍ ብልሃት ተዛምዶን መመርመር ነው፡፡ጥናቱ ከፊል ሙከራዊ ሲሆን የተካሄደውም በአማራ ክልል ምዕራብ ጎጃም ዞን በገነት አቦ 2ኛና መሠናዶ ት/ቤት የሚማሩ የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ሲሆን፣ይህን ዓላማ ለማሳካትም ፣በቃለ መጠይቅ፣ በቅድመና ድህረ ፈተና መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡የጥናቱን መረጃዎች ለመተንተን መጠናዊ የመረጃ መተንተኛ ስልት በተግባር ላይ ውሏል፡፡ከመረጃዎቹ የተገኙት ውጤቶች የሚያመለክቱት የፅህፈት ክሂል ማስተማሪያ ዘዴውና የተማሪዎች ድርሰት የመፃፍ ብልሃት ጋር ዝምድና እንዳላቸው ያሳያል፡፡ እንዲሁም በቃለ መጠይቅ ከመምህራን የተገኘው መረጃም እንደሚያመለክተው ተመሣሣይ የሆነ የማሥተማሪያ ዘዴ(ውጤታዊ) በይበልጥ ለማስተማሪያነት እንደሚጠቀሙ ገልፀዋል፡፡በተመሣሣይ የቅድመና ድህረ ትምህርት ድርሰት የመፃፍ ፈተና የተሰጠ ሲሆን፣ቅድመ ፈተናው ተማሪዎቹ ከሙከራ ጥናቱ በፊት ያላቸውን ድርሰት የመፃፍ ስልት ውጤት ተቀራራቢ መሆን አለመሆኑን ለመፈተሽ ሲሆን፣ የድህረ ፈተናው ዓላማ ደግሞ የሙከራና የቁጥጥር ቡድን ሆነው የተመረጡት ተማሪዎች በተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎች ድርሰት የመፃፍ ስልታቸውን ከተማሩ በሁዋላ በመካከላቸው ውጤት ላይ ጉልህ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለመፈተሽ ነው፡፡በቅድመ ትምህርት የድርሰት መፃፍ ውጤት በሙከራና በቁጥጥር ቡድኖች ላይ ተቀራራቢነት ያላቸው ሲሆን፣በድህረ ትምህርት ድርሰት የመፃፍ ውጤት ግን ጉልህ የሆነ ልዩነትን አሳይቷል፡፡ይህም የሆነበት ምክንያት ሁለቱ ቡድኖች የተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ተጠቅመው ልምምድ ማድረጋቸው ውጤታቸው የበለጠ እንዲሻሻል አድርጎታል፡፡ በመሆኑም መምህራን የተለያዩ የፅህፈት ክሂል ማስተማሪያ ዘዴዎችን እየተጠቀሙ ቢያስተምሩ፣የተማሪዎችን ድርሰት የመፃፍ ብልሃታቸውን ማሣደግ እንደሚቻል ጥናቱ አመላክቷል፡፡

## መግቢያ


ማረጋገጫ........IV
ምስጋና........V
አጠቃሎ........VI
መግቢያ........VII
የሠንጠረዥ ማውጫ........IX
አርዕስት........IX
ምዕራፍ አንድ........1
1.መግቢያ........1
1.1.የጥናቱ ዳራ........1
1.2.የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት........3
1.3 የጥናቱ መሪ ጥያቄዎች........4
1.4 የጥናቱ ዓላማ........4
1.5.የጥናቱ ጠቀሜታ........4
1.6 የጥናቱ ወሰን........5
ምዕራፍ ሁለት........6
ክለሣ ድርሣን........6
2.የጽንሰ ሀሳብ መነሻዎች........6
2.1. የፅሀፊት ምንነት........6
2.2 የፅሀፊት (የድርሰት) ትምህርት አስፈላጊነት........7
2.3 የፅሀፊት ክሂልን የማቀድና የማስተማር መርሆዎች........8
2.4 የፅሀፊትን ክሂል የማስተማር ዘዴ........9
2.4.1 የፅሀፊት ትምህርት አቀራረብ ዘዴዎች........10
2.5.የፅሀፊት ትምህርት ማለማመጃ ተግባራት........15
2.5.1 ተግባር ምዕክል የፅሀፊት መለማመጃዎች........16
2.5.7.1 በክፍል ውስጥ የፅሕፊት ትምህርት ወቅት የመምህሩ ስራና ሃላፊነት........20
2.6 የጥሩ ፅሀፊት መመዘኛ መስፈርቶች........23
2.7 የብልሃት ምንነት ........Error! Bookmark not defined.
2.7.1 የብልሃት አከፋፈል........25
2.8.2 ድርሰት የመፃፍ ብልሀት........26
ምዕራፍ ሦስት........30
3. የአጠናን ዘዴ........30
3.2 የተጠኝዎች ተማሪዎች ናሙና አመራረጥ........30
3.2 1 የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ........30
3.2.2 የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ........31
3.2.3 የመምህራን ናሙና አመራረጥ........31
3.3 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች........31
3.3.2 ቃለ መጠይቅ........31
3.3 3 ፈተና........31
3.4የመረጃ አተናተን ዘዴ........34
4.1የመረጃ ትንተና የውጤት ማብራሪያ........37

4.2. ከመምህራን ቃለ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና ....................................41
ምዕራፍ አምስት .................................................................................... 48
ማጠቃለያና አስተያየት ..............................................................................48
5.1. ማጠቃለያ ........................................................................................48
5.2 አስተያየት ........................................................................................49
ዋቢ ፅሁፎች......................................................................................... 51

አባሪ አንድ ..........................................................................................55

## የሠንጠረዥ ማውጫ

## አርዕስት

ሠንጠረዥ 1:- የቁጥጥርና የሙከራ ቡድኖች ከቅድመ ትምህርት ፈተና የተገኙ ውጤቶች ትንተና---------------36
ሠንጠረዥ 2:- የቁጥጥር ቡድኑ የቅድመና የድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት ንፅፅር ትንተና-----------------------37
ሠንጠረዥ 3:- የሙከራ ቡድኑ የቅድመና የድህረ ትምህርት የፈተና ውጤት ንፅፅር ትንተና-----------------------38
ሠንጠረዥ 4:- የቁጥጥርና የሙከራ ቡድኖች የቅድመና የድህረ ትምህርት ፈተና፡ከይዘት፣ ከአደረጃጀት፣ከስርዓተ ነጥብ አጠቃቀምና ከቃላት ምርጫ አንፃር ትንተና-----------------------------------------------------------------------39

# ምዕራፍ አንድ

## 1.መግቢያ

### 1.1.የጥናቱ ዳራ

ከቋንቋ ክሂሎች ውስጥ አንዱ መጻፍ ነው፡፡ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ የመጻፍ ክሂልን ለማስተማር ደግሞ ብዙ ተግባራትን መወጣት ይጠይቃል፡፡ የሀሳብ አደረጃጀት፣ የቃላት አመራረጥና አጠቃቀም እንዲሁም የዓረፍተ ነገር አወቃቀር እና የአንቀጽ አመሰራረት ለክሂሉ በዋነኝነት ከሚያስፈልጉ ጉዳዮች ውስጥ የሚጠቀሱ ናቸው:: የፅህፈት ክሂልን በትምህርትነት መስጠት ከተጀመረ ጊዜ አንስቶ የተለያዩ የመጻፍ ትምህርት አቀራረቦች አገልግሎት ላይ ውለዋል፡፡ የመጀመሪያው ውጤት ተኮር አቀራረብ ሲሆን፣ ቀደም ባሉት ጊዜያት በተለይም በ1960ዎቹ አካባቢ በስፋት ሲተገበር ቆይቷል፡፡ ዋነኛ ዓላማውም ተማሪዎች መዋቅር (የቋንቋ ህግጋት) ላይ ተመስርተው የፅህፈት ክሂልን እንዲማሩ ማስቻል ነው፡፡ በዚህ አቀራረብ፣ የትምህርቱ ዓላማ ከግብ መድረሱ የሚረጋገጠው ተማሪዎች የሚጽፉትን የመጨረሻ ድርሰት በጥልቀት በማየት ነው (Nunan 1989,1991 ) ፡፡ ይህ አቀራረብ ለቅርጽ ሰፊ ትኩረት መስጠቱ፣ ተማሪዎቹ በራሳቸው ልዩ ልዩ ተግባቦታዊ ተግባራትን እየፈጠሩ እንዲለማመዱ የመደረጉ ሁኔታ ዝቅተኛ መሆኑ፣ እንዲሁም የትምህርቱ ሂደት መምህር መራሽ አቀራረብ ላይ መመስረቱ በዋነኝነት በደካማ ጎን የሚነሱበት ነጥቦች ናቸው፡፡ ውጤታዊ የመጻፍ ትምህርት አቀራረብ የተማሪዎችን የተግባቦት ችሎታ ለማሻሻል ያለው ሚና ዝቅተኛ እንደሆነ ከተረጋገጠ በኋላ ሂደታዊ አቀራረብ ሊመጣ ችሏል፡፡ የዚህ አቀራረብ ዋነኛ ትኩረት ምን ተጻፈ? በሚለው የመጨረሻ ውጤት ሳይሆን፣ እንዴት ተጻፈ? በሚለው ሂደት ላይ ነው፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች በስተመጨረሻ ከሚያዘጋጁት ጽሑፍ ይልቅ፣ ጽሑፉን ለማቀነባበር ለሚጠቀሟቸው ልዩ ልዩ ሂደታዊ ተግባራት ትልቅ ዋጋ ይሰጣል፡፡ ተማሪዎች ጽሑፉን ለማቀናበር የሚያልፏቸው ሂደቶች ለውጤታቸው ማማር ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚያደርጉ ይታሰባል፡፡ በትምህርቱ ሂደት የመምህሩ የበላይነት እና ጣልቃገብነት ሳይኖር፣ ተማሪዎች በራሳቸው የመማር ፍጥነት እየተለማመዱ የመጻፍ ሥራቸውን ያከናውናሉ እንጂ፣ የቋንቋውን ሰዋስዋዊ ህግጋት እንዲያስቡ (እንዲያጤኑ) የሚያደርግ አይደለም (Raimes 1983፣Nunan 1989፣ Richards 1990 እና Hyland 2003)፡፡

የፅህፈት ክሂል ከተማሪዎች ከፍተኛ የሆነ ጥረትን፣ በተከታታይ በክሂሉ መገልገልን በመማሪያ ክፍልና ከክፍል ውጭ ልምምድ ብዙ ጊዜ ማጥፋትን ይጠይቃል ፡፡ የፅህፈት

ክሂል አዕምሮንና አካልን ማቀናጀት የሚፈልግና ከማሰብ ጋር የተያያዘ ተግባር ሲሆን ፣ በአንድ ጊዜም በርካታ ባህርያቱን ( ለምሳሌ ፣ ይዘቱን ፣ ቅርፁን ፣ ዓላማውን ፣ ተደራሲውን ወ.ዘ.ተ ከግምት ውስጥ ማስገባትን የሚጠይቅ ስራ ነው(Byren , 1991,4)፡፡ በፅሄፈውና በአንባቢው መካከልም በሌሎቹ ተግባቦታዊ ዘዴዎች፣ ማለትም በአካልና እንቅስቃሴ፣ በፊት ገፅታ ፣ በድምፅ ከፍታና ዝቅታ፣ የማይጠቀም በመሆኑ ስነ-ልቦናዊ፣ስነ-ልሳናዊና ስነ-አዕምሯዊ ችግሮች የሚከሰቱበት ነው (Byren , 1991,4)፡፡ እነዚህ ባህርያቱ ደግሞ ክሂሉን በመማር ማስተማሩ ሂደትና ውጤታማነት ላይ የየራሳቸውን ተፅዕኖ እንደሚያሳድሩ መገመት ይቻላል ፡፡

በፅህፈት ክሂል የመገልገል ችሎታ እንዲዳብር ለትምህርቱ ትኩረት መስጠት ፣ በቂ ዝግጅትና ልምምድ ማድረግ እንደሚያስፈልግ Norrish ( 1990፡ 63) ይገልፃሉ ፡፡ መምህራን የፅህፈት ክሂልን በማስተማር ወቅት ፅህፈት መማርን ማመቻቸትና መከታተል ፣ የተማሪዎች የፅሁፍ ተግባቦታዊ ክህሎት ማዳበር ፣ የተማሪዎችን ፅሁፍ ማንበብና መገምገም፣ በአፃፃፍ ሂደት ተማሪዎች በማሰላሰል ፣ በማቀድ፣ በማርቀቅና በመከለስ እንዲያልፉ ማድረግ እንደሚጠበቅባቸው Hedge(1991:11) እና Leki (1996:57) ያስገነዝባሉ፡፡Rechards

(1990፡11) በበኩላቸው "መምህራን ተማሪዎች ትክክለኛ ፅሁፍ እንዲፅፉ ማድረግ ብቻ ሣይሆን ተማሪዎች የተዋጣለት የመፃፍ ብልሃት ለመከታተል እንዲችሉ ነገሮችን ማደራጀትና ሁኔታዎችን ማመቻቸት አለባቸው " ይላሉ፡፡ ተማሪዎች በክሂሉ በቂ ዕውቀት አግኝተው ፅህፈትን (ድርሰትን) በቅርፅና በይዘቱ የተሟላ ሊያደርግ የሚችለውን የአፃፃፍ ብልሃት አውቀው መፃፍ እንዲችሉ መምህራን የተለያዩ የፅህፈት ክሂል ማስተማሪያ ዘዴዎችን ቢጠቀሙ ያቀዱት ውጤት ላይ ሊደርሱ ይችላሉ ፡፡ የክሂሉን የማስተማር ዘዴ በተመለከተ አስቴር ( 1998 ) መምህራን ፅህፈትን በማስተማር ዓላማ ተማሪዎችን በማቀድ ፣ በመከለስ ፣ በማርቀቅና በማረም ሂደት እንዲያልፉ ክትትል እንደማያደርጉና የሚሰጧቸውም ድጋፍ እንደሌለ ትገልፃለች፡፡ ሰይድ ( 1993) ደግሞ በፅህፈት ትምህርት ጊዜ ተማሪዎች በመወያየት ፣ ማስታወሻ በመያዝ ፣ ረቂቅ በመፃፍ ፣የብጤ እርማት በማካሄድ ፣ በመከለስ ፣ በማረምና መልሶ በመፃፍ ተግባራት በንቃት ሲሳተፉ፣ በክፍል ውስጥም የፅሁፍ ተግባራትን በተግባር ( በመፃፍ) ሲለማመዱና ሲማሩ እንዳልታዩ ገልፀዷል ፡፡ ሰለሞን (1991) መምህሩ ፅህፈትን በማስተማር ሂደት መምህር ተኮር ዘዴን ስለሚከተሉ የተማሪዎችን ፍላጎትና ልምድ ለመጠበቅ አይሞክሩም ፡፡

ከላይ ለተዘረዘሩት ችግሮች መንስኤ ለየክፍል ደረጃዎቹ በተዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ መርሃ ትምህርቶች ውስጥ ድርሰት የመፃፍ ክሂልን ለማስተማር የሚያስችሉ ይዘቶች አለመኖራቸው ሣይሆን ፣ በክፍል ፣ ውስጥ ተግባራዊ ማድረጉ ላይ ነው፡፡ ይኸውም በተለያየ ምክንያቶች ለምሳሌ ፡- በአንድ ክፍል ውስጥ በሚማሩ ተማሪዎች ቁጥር መብዛት ፣ ቋንቋውን ለመማር የተመደበው ጊዜ ማነስ፣ በመምህሩ ላይ የስራ ጫና መክበድ ፣ ድርሰት ለማስተማር ፍላጎት አለመኖርና አለማስፃፍ፣ የተፃፈውንም አለማረም ክፍሌ ( 1986)፣ አለማየሁ ( 1986) እና ተስፋየ ( 1986) በማለት የችግሩን ምክንያቶች ይገልፃሉ ፡ ፡ ስለሆነም ከእነዚህ ሁሉ ችግሮች በመነሳት በመምህራኑ የፅህፈትን ክሂል የማስተማሪያ ዘዴና በተማሪዎቹ ድርሰት የመፃፍ ብልሃት መካከል ክፍተት ሊፈጠር እንደሚችል መገመት ይቻላል ፡፡

ይህም አቀራረብ ምንም እንኳን መጻፍ ለዚህ ጥናት መነሻ የሆነዉ ከላይ የተጠቀሱት ጥናቶች በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ዉስጥ የጽህፈትን ክሂል ማስተማር እየተዳከመ መምጣቱንና ተማሪዎችም ሀሳባቸዉን በጽሁፍ የመግለጽችሎታቸዉ በጣም አሳሳቢ ደረጃ ላይ መድረሱን መግለጻቸዉ ነዉ፡፡ ይሁን እንጂ ጥናቶቹ ችግሮቹንና መንስኤዎቻቸዉን ከመዘርዘር በስተቀር በመምህራኑ የማስተማር ዘዴና በተማሪዎቹ የመፃፍ ብልሃት መካከል ምን ያህል ዝምድና እንዳለ ወይም ክፍተት እንደተፈጠረ አልጠቆሙም፡፡ ስለዚህም ጽህፈትን የማስተማር ዘዴና የክፍል ዉስጥ ትግበራ ከተማሪዎች የመጻፍ ብልሀት ጋር ያለዉን ግንኙነት በመፈተሽ በሙከራ ለማረጋገጥ የሚሞከር ሆኗል፡፡

## 1.2.የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

አጥኚው ጥናቱን እንዲያካሂድ መነሻ ምክንያት የሆነው ካለው የስራ ልምድ አኳያ የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ድርሰት የመፃፍ ብልሀታቸውና ግንዛቤያቸው አናሳ ሆኖ በማግኘቱ ምናልባት ችግሩ ከፅህፈት ክሂል ማስተማሪያ ዘዴው ሊሆን ይችላል የሚል እምነት ስላለውና ባደረገው የንባብ ፍተሻም በዚህ ርዕስ ዙሪያ ብዙም የተጠና ጥናት ባለማግኘቱ ነው፡፡ ሌላው ፅህፈትን ለማስተማር እየተተገበረ ያለውን ዘዴና በመማር ማስተማሩ ሂደት የመምህራንንና የተማሪውን ሚና በተመለከተ ያለውን ግንኙነት መገምገምና መግለፅ አስፈላጊ መሆኑ ነው ፡፡ በተጨማሪም ፅህፈትን የማስተማር ዘዴ ወይም የክፍል ውስጥ ትግበራ ከተማሪዎች ድርሰት የመፃፍ ብልሀት ጋር ያለውን ግንኙነት መፈተሽ ክፍተት

ካለም ለመቀራረብ የሚያስችል አቅጣጫን መጠቆም ማስፈለጉ ዋና ዋና የጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶች ናቸው ፡፡

## 1.3 የጥናቱ መሪ ጥያቄዎች

ይህ ጥናት ሲጠናቀቅ የፅህፈት ክሂል ማስተማሪያ ዘዴና የተማሪዎች ድርሰት የመፃፍ ብልሃት ተዛምዶን ለመፈተሽ የቅድመና የድህረ ፈተናዎችን በመጠቀም ለሚከተሉት መሠረታዊ ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣልተብሎይታሰባል፡፡

1.የፅህፈት ክሂል ማስተማሪያ ዘዴውና የተማሪዎች ድርሰት የመፃፍ ብልሃት ዝምድና ይኖረው ይሆን?

2.የፅህፈት ማስተማሪያ ዘዴው የተማሪዎችን ድርሰት የመፃፍ ብልሃት ውጤት ያሻሽል ይሆን? የሚሉ ናቸው፡፡

## 1.4 የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በገነት አቦ 2ኛ መሠናዶ ትምህርት ቤት በፅህፈት ክሂል ማስተማሪያ ዘዴና በተማሪዎች ድርሰት የመፃፍ ብልሃት መካከል ያለውን ግንኙነት መመርመር ነው፡፡

ዝርዝር ዓላማዎቹም የሚከተሉት ናቸው፡፡

✔ .የፅህፈት ክሂል ማስተማሪያ ዘዴውንና የተማሪዎችን ድርሰት የመፃፍ ብልሃት ዝምድና መመርመር፣

✔ .የፅህፈት ክሂል ማስተማሪያ ዘዴው የተማሪዎችን ድርሰት የመፃፍ ብልሃት ውጤት ማሻሻሉን መፈተሽ፣

## 1.5.የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታመናል፡፡

♦.የፅህፈት ክሂል የማስተማር ዘዴ ምን እንደሚመስል በመመርመር የክሂሉትምህርት ወደፊት የሚሻሻልበትን መንገድ ለመምህራንና ለትምህርት ባለሙያዎች የበኩሉን ሃሳብ ያቀርባል፡፡

♦.ለአዳዲስ በዘርፉ ወደፊት ጥናት ለሚያካሂዱጥና አጥኝዎች መነሻና አቅጣጫ ጠቋሚ በመሆን ሊያገለግ ይችላል ፡፡

## 1.6 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በዋናነት ትኩረት አድርጎ የተነሳው በገነት አቦ 2ኛና መሰናዶ ት/ቤት የ11ኛ ክፍል መምህራን የፅህፈትን ክሂል የማስተማር ዘዴና የተማሪዎችን ድርሰት የመፃፍ ብልሃት ዝምድናን መመርመር ሲሆን፣ መምህራን የፅህፈት ክሂል ከፅህፈት ማስተማሪያ ዘዴዎች አንፃር እንዴት እንደሚያስተምሩና ተማሪዎችም የቀረበላቸውን የፅህፈት ክሂል ትምህርት መሠረት በማድረግ ድርሰት የሚፃፉ መሆናቸውን መፈተሽ ላይ የተመሰረተ ነው ፡፡ ሆኖም ጥናቱ የፅህፈትን ክሂል ለመማር ማስተማር መሰናከል የሚሆኑትን ነገሮች በመዘርዘርና ለእያንዳንዳቸውም የመፍትሄ ሀሳብ በመፈለግ ላይ አያተኩርም ፡፡

## ምዕራፍ ሁለት

## ክለሣ ድርሣን

### 2.የጽንሰ ሀሳብ መነሻዎች

### 2.1. የፅህፈት ምንነት

ፅህፈት በዕይታዊ (Visual) ትዕምርቶች / Symbols) ውክልና በመገልገል ሰዎች ሃሳብ የሚለዋወጡበትና ተራክቦ የሚመሰረቱበት ተግባቦታዊ መሳሪያ ነው ፡፡ በመተላለፊያ ስልቱ ዕይታዊ ፣ በአካላዊ ትግበራው አፍላቂ ፣ በተግባቦታዊ ባህሪውም ርቱዕ ክሂል ነው (Widdowson 1978 Harmer 1991 ) :: ፅህፈት በተግባቦታዊ መሳሪያነቱ የተደረሰበትን ወይም የተጨበጠን ዕውቀት ማስተላለፊያ ብቻ ሣይሆን አዲስ ሀሳብን ማፍለቂያ መልዕክትን መቀበያና በትዕምርቶች ቀርፆ ማቆያ መንገድና ብልሀት ነው ( Condon and Buthen , 1997) :: Pincas ( 1982) ፅህፈትን ሲገልፁ በትምህርት አማካኝነት የሚቀሰምና ደረጃውን ጠብቆ ከሚደረግ ተከታታይ ልምምድ የሚገኝ ችሎታ ነው ፡፡ ከዚህ ችሎታ ጋርም ፅህፈት አዕምሮንና እጅን በማስተባበር ሃሳብ በተገቢ ምልክቶችና ቃላት በመወከል ለአንባቢ የግልንም ሆነ የጋራ ገጠመኝን የማካፈል ችሎታ ነው ብለዋል ፡፡ እንዲሁም Jordan (1991 ; 41) ይህንን ሃሳብ ሲያጠናክሩ " ፅህፈት የሰው ልጅ ዕውቀቱን፣ ምኞቱን ፣ ሀሳቡን ወዘተ-- ለመሰሎቹ ለመግለፅ የሚጠቀምበት የሚታይና ተቀባይነት ያለው ምልክት ነው " ይላሉ ፡፡

ፅህፈት ሀሳብን በትምዕርት ወይም በቋንቋ የመወከል ሂደት ነው ፡፡ ሂደቱም አካልንና አዕምሮን በማቀናጀት በአንድ ጊዜ በርካታ ባህሪያቱን ለምሳሌ ይዘትን ፣ የአፃፃፍ ስልትን ፣ የፅሁፍ መዋቅርን ፣ የቃላት ምርጫን ፣ የሃሳብ አንድነትን ፣ ግጥምጥምነትንና ተከታታይነትን ከግምት ውስጥ በማስገባት የሚከናወንና ከማሰብ ጋር የተቆራኘ ውስብስብ የአዕምሮ ስራ ነው/ Nunan , 1989:36/ ::

ከላይ ከቀረበው የምሁራን ሀሳብ መረዳት የሚቻለው ፅህፈት በትምህርት የሚዳብርና በተከታታይ ልምድ በመታገዝ እየጎለበተ የሚሄድ ችሎታ መሆኑንና በዚህም የሰው ልጅ አዕምሮውንና አካሉን በማስተባበር ዕውቀቱን ፣ ገጠመኙን ፣ ሀሳቡንና ውስጣዊ ስሜቱን በተገቢ ድምፃዊ ምልክቶች በመወከል ለመሰሎቹ የሚያስተላልፍበት መንገድ መሆኑን ነው ፡፡

በሌላ በኩል ፅህፈት ሆሄያትን በወረቀት ላይ ከማስፈር ከፍ ያለው በአፅምሮ ውስጥ የሚፈልቀውን ሀሳብ በፅህፈት መልክ አቀነባብሮ ለአንባቢ የመግለፅ ሂደት መሆኑን Bryne (1988.1 ) ጨምረው ገልፀዋል ፡፡ ስለዚህም ፅህፈት ለማንበብ ብቻ ተብሎ በወረቀት ላይ የሚሰፍር ሣይሆን የፀሀፊውን ሀሳብና አመለካከት ለአንባቢ ለማድረስ የሚያስችሉ መልዕክትን በአንባቢ አፅምሮ ውስጥ የሚከሰቱ ስርዓት ባለው መንገድ የሃሳብ ችሎታቸውን ጠብቀው የተቀነባበሩ ዓ.ነገሮችን አቀናጅቶ ማስቀመጥ ማለት ነው ፡፡ በመሆኑም ፅህፈት በተዋረድ በተዋቀሩና አንድነትን በፈጠሩ ዓ.ነገሮች አማካኝነት ከተዋጣለት የመግባባት ደረጃ ላይ ሊያደርስ የሚችል እንጂ የምልክቶች ፣ የቃላትና የዓ.ነገሮች ስብስብ ብቻ እንዳልሆነ መገንዘብ ይቻላል ፡፡

Widdowson (1978;62) በበኩላቸው ፅህፈትን ከንግግር ጋር በማነፃፀር በሚታዩ ስምምነታዊ ትእምርቶች / symbols) የሚገለፅ የቋንቋ ሰዋሰዋዊና ፅሁፋዊ ስርዓት መሆኑን ሲገልፅ Raimes (1983,5) ም በቃላት ውክልና በወረቀት ላይ የሰፈረና ህያው የሆነ ቋንቋ ነው ይላሉ ፡፡ በሁለቱ ምሁራን ብያኔ መሰረት የፅህፈት መለያ ባህሪያቱ ዕይታዊ ምልክትነቱ ፣ ለታላሚው ቋንቋ የአገባብ ስርዓት ተገቢነቱን ፣ በቦታና በጊዜ ሳይወሰን ህያው ሆኖ ሊቆይ መቻሉ ናቸው ፡፡

በአጠቃላይ ፅህፈት በስሜት የሚከናወንና በአጭር ጊዜ የሚጠናቀቅ ስራ አለመሆኑን ፣ በአንፃሩ ጊዜ የሚፈጅ ፣ ከፍተኛ ጥረትን የሚጠይቅ ፣ ሀሳብን መቀበል ፣ መጠየቅና መመርመር በትኩረት ማሰብም የሚያሻው የአፅምሮና የአካል ስራ መሆኑን ከተሰጡት ብያኔዎች መገንዘብ ይቻላል ፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ በመደበኛ ትምህርት ቤት የተማሪዎችን የፅህፈት ችሎታ ለማዳበር የፅህፈት ክሂል ማስተማር አስፈላጊ ይሆናል ፡፡

## 2.2 የፅህፈት (የድርሰት) ትምህርት አስፈላጊነት

ተማሪዎች በት/ቤት ቆይታቸው በፅሁፍ የሚያከናውኗቸው ተግባራት በርካታ ናቸው ፡፡ ስለሆነም የሚሰጧቸውን ፅህፈት ነክ ስራዎች በፅሁፍ አቀነባብረው ና አደራጅተው መስራት እንዲችሉ ፅህፈትን ማስተማር አስፈላጊ መሆኑ ይታመናል ፡፡

ከዚህ አንፃር የፅህፈትን (የድርሰትን ) ትምህርት አስፈላጊነት አስመልክተው የተለያዩ ምሁራን ሀሳቦችን ሰንዝረዋል ፡፡ እነዚህም የሚከተሉት ናቸው ፡፡ Wigand ( 1986,141) " ተማሪው መፃፍ ከመጀመሩ በፊትም ሆነ በሚፅፍበት ጊዜ የፅህፈት ተግባራትን ዓላማ ለይቶ በማወቅ ክሂሉን በአግባቡ መጠቀም እንዲችል በቂ የፅህፈት ትምህርት ያስፈልገዋል ፡፡ በት/ቱም ወቅት ለምን እንደሚፃፍ ፣ ለማን እንደሚፃፍ ፣ እንዴት እንደሚፃፍ በመጠየቅ

እንደሚፃፍበት ዓላማ የመፃፍ ክሂሉን የሚያዳብረው ፅህፈትን ሲማር ነው ” በማለት ፅህፈትን የማስተማር አስፈላጊነት ይገልፃሉ ፡፡ Raimes ( 1983) በበኩላቸው ፅህፈትን መማር ተማሪዎች ሌሎች የት/ት አይነቶችን እንዲማሩ ከማገዙም በላይ የታላሚውን ቋንቋ ሰዋሰዋዊ አገባቦችንና አገላለፆችን ፣ ፈሊጣዊ አባባሎችንና ቃላትን እንዲያውቁ ከመርዳቱም በላይ በተማሪዎች ዘንድ የመማር ተነሳሽነትን ይፈጥራል ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ Venkateswalan ( 1995,1054) ” የፅህፈት ክሂል ትምህርት ተማሪዎች በቃል የሚሰጣቸውን ትምህርት አዳምጠውና የተለያዩ ፅሁፎችን አንብበው ማስታወሻ እንዲይዙና በቤት ስራና በክፍል ውስጥ የሚሰጡትን ፅሁፍ ነክ መልመጃዎች በፅሁፍ አቀነባብረው መግለፅ ያስችላቸዋል ይላሉ ፡፡

እንደ Celce Murcia (1991,236) አገላለፅም ተማሪዎች የፊደልን ቅርፅ ለመለየት ቃላትን መስርተው የቃላትን ምርጫና አጠቃቀም በማወቅ ሀሳባቸውን በተገቢ ቃላትና ዓ.ነገሮች ማስተላለፍ የሚያስችሉበትን የተግባቦት ስርዓት እንዲያውቁ ፅህፈትን ማስተማር ያስፈልጋል ፡፡

ከላይ ከቀረበው የምሁራን ሀሳብ መረዳት የሚቻለው በት/ቤት ፅህፈትን የሚማሩ ተማሪዎች የታላሚውን ቋንቋ ፊደል ከመለየት ጀምረው ሀሳባቸውን በብቃት መግለፅ እስከሚያስችላቸው ሰፊ የፅሁፍ መዋቅር ድረስ መማር የሚያስፈልጋቸው ነው ፡፡

የፅህፈት አስፈላጊነት ሰዎችን ከማግባባቱ ወይም ከቦታና ከጊዜ ውስንነት አገልግሎት መስጠት ከመቻሉ አኳያ ብቻ የሚታይ አይደለም (Raimes , 1983, White and Arndt 1991 ) :: ፅህፈት ከተግባራት መሳሪያነቱ ባሻገር የተለያዩ ዕውቀቶችን መቅሰሚያ የሃሳብ ማሳባሰቢያና ማሳያ ሆኖ ያገለግላል ፡፡ ስለዚህ ፅህፈትን መማር ተማሪዎች የፈረጀ ብዙ አገልግሎቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያስችላል ፡፡

## 2.3 የፅህፈት ክሂልን የማቀድና የማስተማር መርሆዎች

ተማሪዎች በፅሁፍ አማካኝነት ሃሳባቸውን በተገቢው ሁኔታ የመግለፅ ሁኔታን እንዲያሳድጉ ለማድረግ መምህራን የፅህፈት ክሂል በሚያዳብሩና የሰዋሰው የቃላት ችሎታን በሚያጠናክሩ መልመጃዎች ላይ በማተኮር ትምህርቱን ማቅረብ እንዳለባቸውና በትግበራ ሂደቱም የሚከተሉትን መርሆዎች ማስታወስ ተገቢ እንደሚሆን Attkins (1996:11) ይገልጻሉ፡፡

የመፃፍ ክሂል በክፍል ውስጥም ሆነ ውጪ የሚለማመዱት መሆን አለበት፡፡ በክፍል ውሥጥ የሚመደበው ክፍለ ጊዜ ለሰዋሰውና ለቃላት ትምህርት ብቻ ሳይሆን ተማሪዎች

መልመጃዎችን መሰረት በማድረግ የመፃፍ ክሂላቸውን ማዳበር አለባቸው፡፡ በክፍል ውስጥ የሚተገበሩት መልመጃዎች አስደሳችና ለመፃፍ የሚያነሳሱ አላማ ያላቸው የተማሪዎችን የቋንቋ ደረጃ እና ልምዳቸውን ያገናዘበ፣ ሃሳባቸውን በቀላሉ እንዲገልፁ የሚያስችል ለውይይትና በቡድን ለመፃፍ ተስማሚ የሆነ፣ ግልፅ መመሪያዎች ያሉትና የሚያበረታታ እንዲሆን ይፈለጋል፡፡ተማሪዎች እንዲፅፉ ከመነገራቸው በፊት ማነሳሳት በግል፣በጥንድ ወይም በቡድን እንዲሰሩ ከተፈለገ በቅድሚያ በግልፅ ሊነገራቸው ይገባል።መልመጃዎች ሲከናወኑ መቆጣጠርያስፈልጋል፡፡ በቁጥጥር ወቅት ጠቃሚና ገንቢ ምጋቤ ምላሽ (feed back)መስጠት፡፡ ለምሳሌ ከፍተኛ ጥረት በማድረግ ላይ ያሉትን መለየት ድጋፍ መስጠት፣ ማድነቅና ማበረታታት፣ፅሁፋቸውን ማረም፣አስተያየት መስጠት፡፡ተማሪዎች መፃፍ የሚፈልጉባቸውን ሃሳቦች በመቀበል በተቻለ መጠን ግልፅና ትክክል በሆነ መንገድ ሃሳባቸውን እንዲገልፁ ማበረታታት፣ተማሪዎች ሃሳባቸውን በፅሁፍ የመግለፅ ችሎታቸው ከተፈለገው ደረጃ ላይ ከደረሰ ሊፈትኑ የሚችሉ አዝናኝና ልቅ ያልሆኑ ውሥን መልመጃዎች ማቅረብና፣ተማሪዎች እርስ በርሳቸው እንዲፅፉ ማበረታታት፣የጻፉትን ፅሁፍ ተቀያይረው እንዲያነቡና አስተያየት መስጠት ማድረግ የሚሉ ይገኙበታል።

### 2.4 የፅህፈትን ክሂል የማስተማር ዘዴ

የማስተማር ዘዴ መምህራን የትምህርት አይነቱን ለተማሪዎች የሚያስተላልፉበት ዕውቀት እንዲጨብጡ የሚረዱበት ፣ ክህሎትን ፣ አመለካከትን ፣ ልምድንና ባህሪይን የሚያዳብሩበት ፣ ተማሪዎችን ከውጫዊ ሁኔታ ጋር የሚያስተዋውቁበት ዘዴ ነው(Azeb 1984) :: ስለዚህም የማስተማር ዘዴ በራሱ ለውጥ የሚያመጣ ሳይሆን ዕውቀትን ለማስጨበጥ የሚረዳ ፣ መምህሩ የሚያስፈልገው ዕውቀት ለማስተላለፍ የሚጠበቅበት መንገድ ነው ፡፡ ጥሩ የማስተማር ዘዴ ተማሪዎች ለሚማሩት ትምህርት ትኩረት ሰጥተው እንዲከታተሉና የሚፈለገው የባህሪይ ለውጥ እንዲመጣ እገዛ ሊያደርግ ይችላል ፡፡

የማስተማሪያ ዘዴዎችን አጠቃቀም አስመልክተው Larson (1986, ) ሲገልፁ ዋናው ነገር አንዱን የማስተማሪያ ዘዴ ከሌላው የመምረጥ ጉዳይ ሳይሆን እንደ አመቺነቱ ለመጠቀም እያንዳንዱ ዘዴ በሚገባ ማወቅ ጠቃሚ ነው ይላሉ ፡፡ በአንፃሩ Richards ( 1985,16) እና Raimes (1983,10) ፅህፈትን ለማስተማር ተገቢ የሆነውን የማስተማር ዘዴ ለመምረጥ አስቸጋሪ መሆኑን ይገልፃሉ ፡፡

Prabu (1990,161-163) በበኩላቸው ጥሩ የማስተማሪያ ዘዴ ነው የሚባለው ጥሩ የመማሪያ ዘዴ ሊሆን ይችላል በማለት የተሻለ ዘዴን የመምረጥን አስቸጋሪነት ይጠቀማሉ ፡፡

ምክንያቱም የእያንዳንዱን ዘዴ አተገባበር ሊወሰኑ የሚችሉ የተለያዩ ተላውጦዎች (Vasiables) ስላሉ ነው ፡፡

ለምሳሌ ፦ ቋንቋው የሚነገርበት ማህበራዊ አውድ ፣ የቋንቋው ትምህርት አላማ ፣ ትምህርቱ የሚሰጥበት የጊዜ መጠን ፣ በአንድ ክፍል የሚማሩ ተማሪዎች ብዛት ፣ ስነ-ልሳናዊ ፣ ስነ ልቦናዊና አዕምሮታዊ ችግሮች ፣ የተማሪዎች ጥሩ የተለያየ መሆኑ አንዱ ዘዴ በሁሉም ሁኔታዎችና ቦታዎች ላይ በብቃት ሊያገለግል አለመቻሉ ነው ፡፡ ስለዚህም መምህራን የማስተማሪያ ዘዴዎቻቸውንና የሚያስተምሩበትን ክፍል ተማሪዎች ሁኔታ በማጥናት የተማሪዎቻቸውን የፅህፈት ክሂል ለማዳበር አመቺ የሆነውን ማስተማሪያ ዘዴ በመምረጥ ማስተማር ይጠበቅባቸዋል ፡፡

### 2.4.1 የፅህፈት ትምህርት አቀራረብ ዘዴዎች

የፅህፈትን ክሂል ለማስተማር የሚያገለግሉ የተለያዩ የአቀራረብ ዘዴዎች ቢኖሩም በአሁኑ ጊዜ ግን ተቀባይነትን አግኝተው በስፋት እየተሰራባቸው ያሉት ሁለት መሆናቸውን የተለያዩ ምሁራን ይገልፃሉ ፡፡ እነዚህም ውጤታዊ አቀራረብ (product Approad ) እና ሂደታዊ አቀራረብ /process approach ) ናቸው ፡፡ (Raimes , 1983, Brown , 1994 , Richards , 1990 Leki , 1996 , Silva 1990 ) ::

#### *2.4.1.1 ውጤታዊ አቀራረብ/ product Approach)*

*ውጤታዊ አቀራረብ ከረጅም ጊዜ አንስቶ ፅህፈትን ( ድርሰትን ) በማስተማር ሂደት ሲያገለግል የኖረና በአሁኑ ጊዜም ለተለያዩ አላማዎች በማገልገል ላይ ያለ ነው ፡፡ ይህ አቀራረብ ትኩረት የሚያደርገው ተማሪዎች በሚፅፉት ድርሰት የመጨረሻ ውጤትና በቋንቋው ቅርፅ ላይ ነው ( Richards , 1990 ) ::*

ይኸውም ተማሪዎች ለሚፅፏቸው ድርሰቶች ምሳሌ ይሆናሉ ወይም ጥሩ ተፅፈዋል ተብለው የሚታሰቡ ፅሁፎችን በሞዴልነት አቅርቦ ሰዋሰዋዊ ህጎችን ፣ አደረጃጀቶችን ፣ የአፃፃፍ ብልሃትን ፣ ወ.ዘ.ተ በማሳየት ተማሪዎች እነዚያኑን አስመስለው እንዲፅፉ የሚያለማምድ ነው ( Nunan 1989,36 እና Richards 1990,106)፡፡ በዚህ ዘዴ ዓላማ መሰረት ተማሪዎች የሚፃፍ የሰዋሰው ፣ የስርዓት ፊደልና ሌሎች ስህተቶቻቸውን ለማስተካከል ሲሆንና በአብዛኛው በክፍል ውስጥ ተማሪዎች የሚያከናውኗቸው የፅህፈት ተግባራት በቋንቋው ሰዋሰው ላይ ያተኮሩ ናቸው ፡፡

ተማሪዎች በሞዴልነት በቀረበው ፅሁፍ ውስጥ ያታን ፣ ጊዜን ፣ ቁጥርን ፣ ወ.ዘ.ተ በመቀያየር የሚለማመዱባቸው ጠቃሚ መልመጃዎች ይቀርባሉ ፡፡ በመምህሩ ተመርጦ በሚሰጣቸው ርዕስ ድርሰት ሲፅፉ መጀመሪያ ትኩረታቸውን በቋንቋው መዋቅር ላይ

እንዲያደርጉ ይጠበቃል ፡፡ ሰዋሰዋዊ ስህተቶቻቸውንም ለማስወገድ ሲሉ በቋንቋው አጠቃቀም ላይ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ይደረጋል ( Leki , 1996) ::

ከፍተኛ ደረጃ ላይ ለሚገኙ ተማሪዎች የዚህ አቀራረብ ዘዴ ትኩረት የሚያደርገው በተለያዩ አንቀፆችና አውዶች መዋቅርና አደረጃጀት ላይ ነው ፡፡ ዓላማውም ትክክለኛ ፅሁፎችን ( ድርሰቶችን ) ማፍለቅ ነው ፡፡ ዋና ዋና ባህሪያቱና መርሆዎቹ የሚከተሉት መሆናቸውን Richards (1990 , 30-32) ይገልፃሉ ፡፡

የድርሰት አፃፃፍ መመሪያዎቻችንና የሰዋሰው ህጎችን በተለያዩ የድርሰት አይነቶች እንዴት መጠቀም እንደሚቻል በማሳየት ተማሪዎቹ በተግባር እንዲለማመዷቸው ያደርጋል ፡፡ የፅህፈት ዓላማ ተማሪዎች በት/ት ተቋም ወይም በግል የሚተገብሯቸውን አይነቶች ቅርፅና አደረጃጀት ላይ ያተኩራል ፡፡ ትክክለኛ የዓ.ነገር መዋቅር መስራት የትምህርቱ አስፈላጊ አካል ነው ፡፡ ስለዚህም የሰዋሰው ችሎታ ከፍተኛውን ቦታ ይይዛል ፡፡ሞዴሎችን በማቅረብ ተማሪዎች አስመስለው እንዲፅፉና ስህተት እንዳይሰሩ ለማድረግ ይሞክራል ፡፡የእጅ ፅሁፍ ፣ የስርዓተ ነጥብ ፣ የቃላት አገባብ ፣ የፊደል አጣጣል ወ.ዘ.ተ እውቀቶች በትምህርት ይሰጣሉ ፡ ፡

### 2.4.1.1.1 የውጤታዊ አቀራረብ የፅህፈት ደረጃ

በውጤታዊ አቀራረብ ፅህፈትን በማስተማር ሂደት በየደረጃው የተለያዩ ተግባራት ይከናወናሉ ፡፡ እነዚህም ተግባራት ውስን ፅህፈት ፣ ምር ፅህፈትና ነፃ ፅህፈት ደረጃዎች ናቸው (Pincas ፣ 1982፣ 14፣ Raimes ፣1983 ,7 Richards , 1990,107 )

**ሀ. ውስን ፅህፈት** ( Contrplled Writing )

ለመጀመሪያ ደረጃ የቋንቋ ትምህርት ተማሪዎች ለማካሄድ የፅህፈት ትምህርት የሚቀርብና የውስንነት ደረጃው ፍፁም ወይም አንፃራዊ የሆነ ክንውን ነው ፡፡ የዚህ የፅህፈት ስራ ዋና ዓላማ ተማሪዎች አንፃራዊ በሆነ መንገድ ከስህተት የፀዳ ፅሁፍ እንዲፃፍ ማድረግ ነው ፡፡ በውስን የፅህፈት ደረጃ ፅህፈትን ለማስተማር የሚቀርቡት ይዘቶች ውስን ማሰብንና ማፍለቅን የሚጠይቁ ናቸው ፡፡ በውስን ፅህፈት ደረጃ ባዶ ቦታዎችን መሙላት ፣ በሠንጠረዥ የቀረቡ ቃላትን በማቀናጀት ዓ.ነገር መስራት ፣ቅደም ተከተላቸው የተፋለሰ ቃላትን በማስተካከል ዓ.ነገር መስራት ፣ በአንቀጽ ውስጥ ፣ የቁጥር፣ የፆታ ፣ የጊዜ ወ.ዘ.ተ ለውጥ በማድረግ እንደገና መፃፍ የመሳሰሉት ይገባቸዋል ( Doff ፣ 1988 እና ( Kroll) ፡፡

### ለ. መር ፅሀፈት ( Guided Writing )

መር ፅሀፈት በውስንና በልቅ ፅሀፈት መካከል እንደ ድልድይ ሆኖ የሚያገለግል ነው ፡፡ ይኸውም ተማሪዎች በውሱን ፅሀፈት ደረጃ ካዳበሩት መሰረታዊ የዓ.ነገር የአፃፃፍ ክሂል በተጨማሪ የአፃፃፍ ስልት ለመለየት የሚያግዙና ወደ ነፃ ( Free Writing ) የሚያሸጋግሩ ይዘቶችን የሚይዝ በመሆኑ ነው ፡፡ በዚህ ደረጃ ተማሪዎች መምህራን በሚያቀርቡላቸው ሞዴል መሰረት የፅሀፈት ልምድ ያደርጋሉ ፡፡ በዚህ ደረጃ የሚካሄዱ ውይይቶች ድርሰትን ለመፃፍ የሚያገለግሉ ምር የፅሀፈት ተግባራት መሆናቸውን Doff (1988,) 62) Raimes ( 1983 , 103 ) እና Pincas (1982፣102 ) ይገልፃሉ ፡፡

### ሐ. ነፃ ( ልቅ ( Free Writing )

በዚህ ደረጃ ተማሪዎች በአብዛኛው መምህራን በሚሰጧቸው ወይም ራሳቸው በመረጡት ርዕስ ዙሪያ ሀሳብ አፍልቀው በራሳቸው ቋንቋና አገላለፅ ድርሰት የሚፃፍበት ነው ( Pincas , 1982 እና Raimes , 1983 ) :: ድርሰት የመፃፍ ስራ የሚጀምረው የቋንቋውን ሰዋሰዋዊ ቅርፆች በመለማመድ ነው ፡፡ ከልምምድ ቀጥሎ ለሚፃፉት የድርሰት ዓይነት ሞዴል ይቀርባል። ነፃ ፅሀፈት ለሰዋሰዋዊ አጠቃቀም እና ለስርዓተ አፃፃፍ ትኩረት የሚሰጥ ፣ እንዲሁም በትክክለኛነት ላይ የሚያተኩር ቢሆንም ፣ ተማሪዎች የራሳቸውን ሀሳብ የሚገልፁበት እድል ይሰጣል ፡፡ Raimes (1983,7) ነፃ ፅሀፈት ተማሪዎች ሀሳባቸውን ለመግለፅ የሚፅፉበት ደረጃ ቢሆንም የፅሁፋቸው መለኪያ ምን ፣ እንዴት ፣ ለማንና ለምን ተፃፈ ? የሚሉት ጥያቄዎች ሳይሆኑ የሚነሱት ሰዋሰዋዊ ስህተቶች ያልበዙበት ፅሁፍ ቀረበ ወይ ? የሚለው ነው ፡፡ በመሆኑም የተማሪዎቹ ትኩረት የሚያርፈው ሀሳባቸውን በመግለፅ ላይ ሳይሆን ፣ በፅሁፋቸው ጥራት ወይም ንፅህና ላይ ነው ( Byren, 1991 , 16 እና Pincas 1982 ) ::

### 2.4.1.12 በውጤታዊ አቀራረብ የፅሀፈት ማስተማሪያ ዘዴ የመምህሩ ሚና

በአብዛኛው የቋንቋውን ሰዋሰዋዊ ህጎችን ማስተማር ፣ የተማሪዎችን የመጨረሻ ውጤት ሰብስቦ ሰዋሰዋዊ ስህተቶችንና የአፃፃፍ ስርአተ ግድፈቶችን ማረም ፣ የፅሁፉን ጥሩነትና መጥፎነት ከትክክለኛነት አንፃር መገምገም ፣ ለመማር የሚያበረታታ አስተያየት ወይም ውጤት መስጠት ነው።በውጤታዊ አቀራረብ ፅሀፈትን ለማስተማር የሚዘጋጅ መምህር ተማሪዎች ውጤታማ እንዲሆኑ ተገቢውን ዝግጅት ሊያደርግ እንደሚገባ Byrne (1988) Pincas (1982) Atkins እና ሌሎች ( 1995) የሚከተሉትን ነጥቦች በመዘርዘር ይገልፃሉ ፡፡

1. ለፅህፈት ክሂል የተመረጡት መልመጃዎች ለተማሪዎች ቀርበው ከመተግበራቸው በፊት ተገቢነታቸውን ፣ ቀስቃሽነታቸውን ፣ ግልፅነታቸውንና ለአውዱ ተገቢ መሆናቸውን ያረጋግጣል ፡፡

2. መልመጃዎች ግልፅ መመሪያ ያላቸውና ከሌሎች ክሂሎች ጋር ቅንጅት ያላቸው መሆኑ ያሳውቃል ፡፡

3. የቋንቋውን ሰዋሰዋዊ ህግጋት ለተማሪዎች በማሳወቅ በፅሁፋቸው ውስጥ እንዲጠቀሙ ያደርጋል ፡፡

4. ተማሪዎች ለፅህፈት ትምህርት ቅድመ ዝግጅቶች የሚያደርጉበትን ሁኔታ ያመቻቻል ፡፡

### *2.4.1.2 ሂደታዊ አቀራረብ / Process Approach)*

በዚህ የአቀራረብ ስልት ትኩረት የሚያደርገው በድርሰቱ የመጨረሻ ውጤት ላይ ሳይሆን ከመጀመሪያው ጀምሮ በፅህፈት ወቅት በሚከናወኑት ተግባራት ወይም ወደ ውጤት ለማድረስ በሚያስችለው ሂደት ላይ ነው ፡፡ በሂደታዊ አቀራረብ የፀሀፊው ትኩረት ስለሚሃፊው ፅሁፍ ዓላማና ስለተደራሲዎቹ ሣይሆን ፣ ፅሁፉን እንዴት እንደሚጀምርና እንዴት እንደሚያደራጀው በመወሰን ላይ ነው ( Raimes , 1983 ,10)፡፡

በመማር ማስተማር ሂደትም የመምህራን የበላይነትና ጣልቃ ገብነት ሳይኖር ተማሪዎቹ በራሳቸው የመማር ፍጥነት እንዲለማመዱ ፣ ስለሚፅፉት ድርሰት የአፃፃፍ ሂደት እንጂ የቋንቋውን ሰዋሰዋዊ ህግጋት እንዲያስቡ እድል አይሰጥም ( Silva , 1990 )፡፡ ሂደታዊ የፅህፈት ትምህርት አቀራረብ እንደ ውጤታዊ አቀራረብ ከተጠናቀቀ የድርሰት ረቂቅ ላይ እንዲሁም በቋንቋው ቅርፅ ላይ ከማተኮር ይልቅ የመፍጠር ፣ አዲስ ነገር የመፈለግ ፣ ትርጉምን የማስፋፋት ሂደትን የሚከተልና በፅሁፍ ይዘት ( ትርጉም ) ላይ የሚያተኩር ነው ( Rivers , 1981) ::

በሂደት ተኮር የሚያስተምሩ መምህራን ክፍሉ ጥሩ ወይም ምቹ የመፃፊያ አውድ እንዲሆን ማመቻቸትና ተማሪዎችን ማገዝ እንጂ በመፃፍ ወይም በትምህርቱ ላይ ማዕከላዊ ሚና የላቸውም ፡፡

### 2.4.1.2.1 የሂደታዊ አቀራረብ የፅህፈት ደረጃዎች

በሂደታዊ አቀራረብ ፅህፈትን በመማር ማስተማር ሂደት ተማሪዎች በተለያዩ አቀራረብ የፅህፈትን ተግባራትን ለማከናወን ልዩ ልዩ የፅህፈት ደረጃዎችን ያልፋሉ ፡፡

እነዚህ የአፃፃፍ ደረጃዎች Richards ( 1990,112) , Hedge (1988, 22-24) እና Raimes (1983፣69) ቅድመ ፅህፈት ፣ ጊዜ ፅህፈት ፣ እና ድህረ-ፅህፈት በማለት በሶስት ሲከፍሏቸው Dukes (1983) እና Murras (1982) ደግሞ የማሰላሰል ፣ የማርቀቅና የክለሳ ደረጃ በማለት ይገልፃቸዋል ፡፡

*ሀ. ቅድመ ፅህፈት ደረጃ*

ቅድመ ፅህፈት የማሰላሰል ደረጃ ሲሆን ፣ መፃፍን ከመጀመር በፊት የሚከናወኑ ዝግጅቶችን በሙሉ ይይዛል ፡፡ ይኸውም ተማሪዎች ሀሳባቸውን የሚያሰባስቡበት ፣ እቅዳቸውን የሚነድፉበትና በአጠቃላይም ወደ ዋናው የፅህፈት ደረጃ ለመግባት የሚዘጋጁበት ሂደት ነው ፡፡ ስለምን ልፃፍ ? እና እንዴት ልፃፍ ?የሚሉት ጥያቄዎች ምላሽ የሚያገኙት በዚህ ክፍል ነው ፡፡ በዚህ ደረጃ ተማሪዎች በመረጡት ርዕስ ላይ ከክፍል ጓደኞቻቸው ጋር በመሆን ይነጋገራሉ ፡፡ መምህራን ለተማሪዎች መመሪያ በመስጠት የሚፅፉትን ርዕሰ ጉዳይ በሚገባ እንዲያውቁት ይመራሉ ፣ ይከታተላሉ (Murray ., 1982 , Hedge , 1988 እና Richards , 1990 ) ::

**ለ. ጊዜ ፅህፈት**

ጊዜ ፅህፈት የማርቀቅ ደረጃ ሲሆን ፣ በዚህ ደረጃ ሀሳብ በማፍለቅ ጊዜ የተሰበሰቡ መረጃዎችን የማመቻቸትና የመጀመሪያ ረቂቅ መፃፍና የተፃፈውን የማንበብና የመከለስ ፣ ፅሁፍ የሚዳብርበትን ሀሳብ የመፈለግ ተግባር ይከናወናል ፡፡ ተማሪዎች በዚህ ጊዜ ለሰዋሰዋዊ ስህተቶች አይጨነቁም ፣ ሀሳብ እንደመጣላቸው ይፅፋሉ ፣ የማይፈልጉትን ሀሳብ አስወጥተው አዲስ ሀሳብ መተካት ይችላሉ ፡፡ በጊዜ ፅህፈት ቅድሚያ የሚሰጠው ለይዘት ትክክለኛነት ሲሆን ፣ በቀጣይ በሚፅፉት የድርሰት ረቂቅ ላይ ከይዘት ባሻገር ተማሪዎች የተጠቀሙባቸውን ስርዓተ ነጥብ ፣ ሰዋሰውን ፣ የሆሄያት አጣጣልን ፣ ወ.ዘ.ተ የመመርመርና የማስተካከል ተግባርን ያከናውናሉ (Hedge , 1991 ) ::

### ሐ. ድህረ ፅህፈት

ድህረ ፅህፈት የክለሳ ደረጃ ሲሆን ፣ ፀሀፊው የፅሁፉን መልዕክት ፣ ቅርፁንና ተደራሲውን ደግሞ የሚያስብበት ፣ የመልዕክቱን ግልፅነት የሚገመግምበትና የመጨረሻ ማስተካከያ የሚፅፍበት ደረጃ ነው ፡፡ በዚህ ደረጃ ላይ ፀሀፊው በፅሁፍ ውስጥ ለአንባቢያን ያስቸግራሉ የሚላቸውን የተለያዩ ቃላትን ለይቶ በማውጣት ማስተካከያ ይሰጣል ፡፡ የተፃፈውን ፅሁፍ ከሰዋሰው ፣ ከስርዓተ ነጥቦችና ከሀሳብ አደረጃጀት አኳያ የሚመረምርበት በዚህ ደረጃ ነው ፡፡

### 2.4.1.2.2 በሂደታዊ አቀራረብ የፅህፈት ማስተማሪያ ዘዴ የመምህሩ ሚና

በሂደታዊ አቀራረብ ፅህፈትን የሚያስተምር መምህር ለተማሪዎች የእርስ በርስ መማማር ወይም ተራክቦ ቦታውን እንደሚለቅ ጥናቶች ይጠቁማሉ ፡፡ በዚህም መሰረት መምህራን መማርን የማመቻቸትና የመከታተል ፣ የተማሪዎችን የፅሁፍ ተግባቦታዊ ክህሎት የማዳበር ፣ የተማሪዎችን ፅሁፍ የማንበብ ፣ የመገምገምና የማማከር ፣ እንዲማሩ የማገዝ ፣ መማርን የማፋጠን Ruddeg (1999 ) , Scrivene (1994) , Hedge (1991,7) እና Leki (1994,57) ሚና ይጫወታል ፡፡

ሂደታዊ የፅህፈት አቀራረብ በክፍል ውስጥ በሚተገበርበት ጊዜ የመምህሩን የማስተማር ዘዴ በተመለከተ Richards (1990,111) የሚከተለውን ሀሳብ ያቀርባሉ ።በሂደታዊ አቀራረብ መምህሩ ተማሪውን እንደ ውጤታዊ አቀራረብ ዘዴ ያለቀለት ስራ እንዲያቀርብ የተወሰነ ነገር የሚጠይቀው ሣይሆን ፣ ተማሪው ትክክለኛ ፅሁፍ ፣ ለመፃፍ የሚያስችለውን ዘዴ የሚቀይስና የሚያመቻች እንደሆነ ይገልፃሉ ፡፡፡

### 2.5.የፅህፈት ትምህርት ማለማመጃ ተግባራት

ተማሪዎች ብዙ በፃፉ ቁጥር ብዙ የመመራመር እና የመማር እድል ስለሚያገኙ የፅህፈትን ጠቃሚነት ያውቃሉ፡፡ ስለዚህ ፅህፈትን በተግባር ማለማመድ የሚያስችሉ መልመጃዎችን አዘጋጅቶ በተከታታይ እንዲሰሩ በተማሪዎች ላይ አዳዲስ ልምዶችን ያካብታል (ኢሳያስ 2002፥9)፡፡ የፅህፈት ትምህርት ተከታታይነት ያለው ልምምድ የሚከተል መርህ ያለው በመሆኑ ተማሪዎች በጥሩ ሁኔታ መፃፍን ይለማመዳሉ፡፡ የፅሁፈት ትምህርትማድረግ ለመለማመድ የሚያግዙ ተግባራት አሉ፡፡ እነዚህም Olishtian (1991)ን፣ Raimes (1993)ን፣ Ur (1996)ን፣ Harmer (1991) መሰረት በማድረግ በሶስት ከፍሎ ማስቀመጥ ይቻላል፡፡ ከዚህ ቀጥሎ እያንዳንዳቸውን ለማየት እንሞክራለን፡፡

### 2.5.1 ተግባር ምዕክል የፅህፈት መለማመጃዎች

ተግባር ምዕክል የፅህፈት ትምህርት መለማመጃ ተግባራት ቅደም ተከተላዊ ይዘት ያላቸው ሲሆኑ፣ መነሻቸው በፊደልና በስነምዕላድ ላይ ነው፡፡ እነዚህን ለማስተማር የተለያዩ ማስታወሻዎች ፣አጫጭር መልዕክቶች፣ቀላል መማሪያዎች ፣ የክፍሉ ስራዎች ፣የግብዣ፣ የሰላምታና የምስጋና ፅሁፎች እንዲለማመዱ ይደረጋል፡፡ (Olishtian 1991:240 ፣ Raimes 1983:83)፡፡

ከዚህ በተጨማሪም የተለያዩ በክፍል ውሥጥ ፅህፈትን ለመለማመድ የሚያስችሉ ተግባራት የያዙ፣ ለፅህፈት ትምህርት አመቺነት ያላቸው ይዘቶች በመጠቀም ማለማመድ ይቻላል፡፡ ለምሳሌ ጅምር ስራዎችን ማጠናቀቅ ፣ የግብይት ዘገባን ማዘጋጀት ወዘተ መጥቀስ ይቻላል፡፡ እነዚህንና የመሳሰሉትን የማለማመጃ ስልቶችን በመጠቀም ተማሪዎች የተለያዩ ፅሁፎችን በክፍል ውስጥ ወይም ከክፍል ውጪ እንዲፅፉ ማድረግ ፍላጎታቸውን ለማነሳሳት ይረዳል፡፡

### *2.5..2 ስሜት ነክ የፅህፈት ማለማመጃዎች*

ሰሜት ነክ የፅህፈት ማለማመጃዎች የተማሪዎቸን የግል ፍላጎት የሚመለከቱ ናቸው፡፡ እነዚህም ደብዳቤ፣የራስ ገጠመኝ እና ልምድ ፣ጉዞ፣የእለት ተዕለት ክንውኖች እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡ በተለይ ለከፍተኛ ክፍል ተማሪዎች ስለራስና ስለጓደኛ ትረካ ፅሁፎችን እንዲያዘጋጁ ማድረግ የተማሪዎች ፍላጎት መሰረት ያደረገ የትምህርት አቀራረብ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡ በመሆኑም በፅህፈት ትምህርት የመማር ማስተማር ሂደት ውሥጥ መምህራን እነዚህን ተግባራት መሰረት አድርገው ማስተማር እንዳለባቸው Olishtian (1991:242)ይጠቁማሉ፡፡

### *2.5..3. ትምህርት ቤት - ተኮር የፅህፈት ማለማመጃዎች*

የተማሪዎች በትምህርት ቤት ይበልጥ ጠቃሚ የሆነው ተግባር ለትምህርት ቤታቸው ሕይወት ይፅፋሉ፡፡ የትምህርት ቤት የመማር-ማስተማር ሂደት የሚከናወነውም ተማሪዎች በሚሰሩዋቸውን የተለያዩ ተግባራት መሰረት በማድረግ ነው፡፡ ከነዚህ ተግባራት መካከል ጥቂቶቹን እንመልከት፤የክፍልና የቤት ስራዎች መፃፍ፤የተለያዩ ጥያቄዎች (ለምሳሌ፡- ማጠቃለያዎችን፣ ለተጠየቁት ጥያቄ መልስ፣ ድርሰት፣ ወዘተ.) መጻፍ፤የገለፃ ማስታወሻዎችን መፃፍ፤የተለያዩ ደብዳቤዎችን (የግል፣የመስሪያ ቤት ፣የስራ ማመልከቻ ) መፃፍ፣የመስክ ጉብኝትን ተጠቅመው ስላዩት ነገር ዘገባ ማቅረብ፤ትምህርት ቤት -ተኮር

የሆኑ ዜናዎችን መፃፍ እና የመሳሰሉት ናቸው።(Ur 1996:164፣ Harmer 1991:143፣ Byrne 1988:23፣ Raimes 183:83)::

በአጠቃላይ ከላይ ከቀረቡት ሃሳቦች እንደምንረዳው ፣ የፅህፈት ትምህርት በትምህርት ቤት የሚማሩት በብዙ መንገድ እንደሆነ ነው፡፡ ከፍ ብሎ በንዑሳን ርዕሶች ከተገለፀው በተጨማሪ ተማሪዎች በትምህርት ቤት ተዛማጅ የትምህርት አይነቶች በመማር ሂደት ፅሁፍን በተዘዋዋሪ መንገድ እየተማሩ እንደሆነ ይጠቁማሉ፡፡

**የፅህፈት ትምህርት ማቅረቢያ ስልቶች**

የፅህፈት ትምህርትን የተለያዩ ማስተማሪያ ስልቶችን በመጠቀም በተሻለ መንገድ ማስተማር ይቻላል፡፡ መምህራን የፅህፈት ክሂልን በሚያስተምሩበት ወቅትም የተማሪዎችን የፅህፈት ክሂል ለማዳበር የሚረዱ ስልቶችን መጠቀም አለባቸው፡፡ ሁሉንም መምህራን ተመሳሳይ የሆነ የፅህፈት ማስተማሪያ ስልቶችን ይጠቀሙ ለማለት ግን አያስደፍርም፡፡ ምክንያቱም መምህራን ፅህፈትን በሚያስተምሩበት ጊዜ የራሳቸው የሆነ የሚከተሉት የማስተማሪያ ስልት ሊኖራቸው ይችላል፡፡ ቢሆንም የተለያዩ የፅህፈት ትምህርትን የማስተማሪያ ስልቶች እንዳሉ Byrne (1988:25) እና Raimes (1983:97) ያስረዳሉ፡፡ ቀጥሎ እንነዚህን የፅህፈት ክሂል የማስተማሪያ ስልቶች ይቀርባሉ፤

### *2.5.4. በአቻ ፅሁፎች አማካኝነት ፅህፈትን ማስተማር*

የተመሳሳይ ፅሁፍ አቅርቦት ተያያዥነት ያላቸውን ፅሁፎች ለማስተማር የሚጠቅም ነው፡፡ ሞዴል ፅሁፎች የተማሪዎችን የትኩረት አቅጣጫ ስለሚስቡ፣የተለያዩ ሰዎችን የአፃፃፍ ስልትን እንዲያውቁ በማድረግ የቀረበላቸውን ሞዴል ፅሁፍ ተመልክተው ቀጥለው ለሚሰሩት ስራዎች በመሰረትነት ይጠቀሙበታል፡፡በተለይ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች በታላሚው ቋንቋ በቂ የንባብ ልምድ ስለሚያደርጉ በክፍል ውሥጥ በመምህሩ አማካኝነት ተመርጠው የሚቀርቡ ሞዴል ፅሁፎች የፅህፈት ችሎታቸውን ያዳብሩላቸዋል፡፡

ቀስ በቀስ ወደ ፅህፈት እንዲሸጋገሩና እንዲለማመዱ ስለሚያበረታቱ ጠቃሚነታቸው የጎላ ይሆናል፡፡ Edge (1992:42) ይህንኑ ሃሳብ በመጋራት "ሞዴል ፅሁፎችን ከፅህፈት ትምህርት ጋር አያይዞ ማቅረብ ጠቃሚ ስልት ነው"ይላሉ፡፡

ተማሪዎች በቀረበላቸው አቻ ፅሁፍ መሰረት ነፃ ፅሁፍን ለመጠቀም የሚያስችላቸው መሆኑን Raimes እንደሚከተለው ይገልጻሉ፤

> አቻ ፅሁፍ ነጻ የሆነ የግደባ ጽሁፍ አይነት ነው፡፡ በቀረበው ሞዴል ጽሁፍ ውስጥ ለውጦችን ከማድረግ እና በቀረቡት ዓረፍተ ነገሮች መሰረት ከመጻፍ ይልቅ

ተማሪዎች የተሰጣቸውን ሞዴል ፅሁፍ በማንበብና ማጥናት ተመሳሳይ በሆነ ርዕሰ ጉዳይ ላይ በራሳቸው ይፅፋሉ፡፡ ለዚህም በቀረቡላቸው ሞዴል ፅሁፍ ውስጥ የሚያገኙዋቸውን ቃላት የዓረፍተ ነገሮችን መዋቅርና አደረጃጀት እንደመመሪያ ይገለገሉባቸዋል (1983፥83፥84)፡፡

በአጠቃላይ አቻዊ የሆኑ ወይም ሞዴል ፅሁፎችን በመጠቀም የተማሪዎችን ፅህፈት ችሎታ ማዳበር ይቻላል፡፡ ተማሪዎች የራሳቸውን ምናባዊ ፈጠራ የሚያክሉበት ሰፊ ነፃነት በመስጠት እንዲሁም ከራሳቸው አመለካከት በመነሳት ስለአንድ ሁኔታ ወይንም ድርጊት እንዲፅፉ ማድረግ ሌላው ስልት ነው፡፡

*2.5.5. በምንባብ አማካኝነት ፅሀፈትን ማስተማር*

በፅህፈት ክሂል ትምህርት ውጤት በማስገኘት ምንባብ አብዛኛውን ጊዜ አስፈላጊ ነው፡፡ ይህንን ሃሳብ (1988፥17) የፅህፈትን ችሎታ በማዳበር ረገድ፣ምንባብ እጅግ በጣም ከፍተኛ ሚና እንዳለው ያብራራሉ፡፡ ምክንያቱም ብቻውን ጥሩ ፀሃፊዎችን ማምረት ባይቻልም፤በጣም አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታ ይፈጥራል፡፡

በምንባብና በፅህፈት መካከል ያለውን ግንኙነት ሲገልፅም፣ ሌሎች ፀሃፊዎች ከፃፉዋቸው ምንባቦች ጋር የንባብ ግንኙነት ያላቸው ተማሪዎች፣ ስለፅሕፈትም ብዙ ነገሮችን መማር ይችላሉ" ይላሉ፡፡ከዚህ ሃሳብ እንደምንረዳው ከምንባቦች ጋር ከሚኖራቸው ግንኙነት፣ ተማሪዎች ከንባቡ በኋላ ላይ የራሳቸውን ፅሁፍ ለማዘጋጀት የሚያስችላቸውን አንዳንድ የአፃፃፍ ስልቶችንና የአፃፃፍ ስርዓቶችን ያገኙበታል፡፡

በመሆኑም ተማሪዎች ለፅህፈት ትምህርት በማነሳሳት በኩል ምንባቦች ከፍተኛ ጠቀሜታ አላቸው፡፡ ስለዚህ ለተማሪዎች የሚቀርቡ የምንባብ ይዘቶች ጥሩ የሆኑ የፅህፈት ተግባቦትን ለመፍጠር የሚያስችሉ፣ አዳዲስና ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎችን የሚያስተላልፉ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

## *2.5.6 ስዕሎችን በመጠቀም ፅሁፎችን ማስተማር*

ስዕሎችን በዓይን በማየት ከምንማርባቸው መሳሪያዎች መካከል ግንባር ቀደም ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ምክንያቱም በፅህፈት ትምህርት ውስጥ ተስማሚ አውድን ለመፍጠር ጥሩ ምንጮች ናቸውና፡፡ በሌላ አገላለፅ ስዕሎች በመማር ማስተማር ሂደት ውሥጥ በተማሪዎች ላይ የአፃፃፍ ልዩነቶችን ሊፈጥሩ ይችላሉ፡፡ እንዲሁም ብቁ የፅህፈት ስራ ለማዘጋጀት ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር ይረዳሉ፡፡ ስለዚህ በፅህፈት ትምህርት ጊዜ ከቀላል ዓረፍተነገሮች ቅንጅት እስከ ከባድ የፅህፈት ስራ ያለውን ችሎታ ሽፋን ይሰጣሉ፡፡ፅህፈትን ለማስተማር በስዕሎች የመጠቀም ፋይዳን አስመልክቶ Raimes (1983:84) ሲገልፁ፣እንደሚከተለው ያስቀምጡታል፤

> *ስዕሎች ከክፍል ውጭ የሚኖረውን ሁኔታ ወደ ክፍል ለማምጣት የሚረዱ ምንጮች ናቸው፡፡ ምክንያቱም ስዕሎች የክፍል ውስጥ ልምድ ልውውጦችን፣የጋራ የሆኑ የቋንቋ ቅርፆችን የመጠቀም ፍላጎት ፣ ወዘተ፣ የተማሪዎችን የፍላጎት ትኩረት ያሳያሉ፡፡*

ጠቅለል አድርገን ስንመለከተው፣ ስዕሎች የፅህፈት ትምህርትን ለማስተማር አጋዥና ተማሪዎቸን ለፅህፈት ትምህርት በማነሳሳት በኩል ጠቀሜታ ያላቸው ናቸው፡፡

## *2.5.7 ከሌሎች ክሂሎች ጋር በማቀናጀት ፅህፈትን ማስተማር*

የቋንቋ ትምህርት በሚቀርብበት ወቅት የክሂል ትምህርቶች እርስ በርስ የመደጋገፍ ባህርይ ስላላቸው አንዱን ክሂል ከሌላው ክሂል ነጥሎ ማቅረብ በጣም አስቸጋሪ ነው (አስቻለው 2000፡47)፡፡ ከዚህ በተጨማሪ Harmer (1991:52) እንደሚጠቁሙት ፣ የክሂል ትምህርቶችን በተናጠል ለተማሪዎች አንድ ቀን ንባብን ፣ በሌላ ቀን ንግግርን ብቻ ማስተማር ሊሆን የማይችልና የማይታመን ነው፡፡ ይኸውም አንድን ክሂል ለብቻው ነጥሎ ማቅረብ የማይቻል መሆኑን ያመለክታል፡፡ ሰዎች አብዛኛውን ጊዜ ወደ ፅሁፍ ከመግባታቸው በፊት ያነባሉ፤ያነበቡትን መሰረት በማድረግ ለመፃፍ ይነሳሉ፡፡ በተጨማሪም አንድ ሰው ገለፃ በሚያደርግበት ወቅት እያዳመጡ ማስታወሻ ይይዛሉ፡፡ በመቀጠልም የቀረበውን ገለጻ በዘገባ መልክ ሊያቀርቡት ይችላሉ፡፡

በአጠቃላይ መምህራን የፅህፈት ትምህርትን በሚያቀርቡበት ጊዜ ተማሪዎች ፅህፈትን ከመለማመዳቸው በፊት ፅሁፎችን እንዲያነቡ፣ በውይይት መልክ ሃሳባቸውን እንዲለዋወጡ ወዘተ ቢያደርጉ መልካም ነው፡፡ በርግጥ ይህንን ስናደርግ የፅህፈት ችሎታን ለማዳበር

አልመን ሊሆን ይችላል፡፡ ቢሆንም አንዱን ክሂል ሲነሳ ሌላው አብሮ የመነሳት ባህርይ ስላለ በታቀደ የቅንጅት ትምህርት ውሥጥ የተሻለ ይሆናል፡፡

### 2.5.7.1 በክፍል ውስጥ የፅሕፈት ትምህርት ወቅት የመምህሩ ስራና ሃላፊነት

ማስተማር የአንድን ነገር ክንውን ወይም አሰራር ማሳየት ወይም ለመስራት መርዳት፣ መመሪያ መስጠት ፣ለማወቅና ለመገንዘብ እና ችሎታን ለማዳበር ምክንያት መሆን ነው፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ የሚማሩት ተማሪዎች በመሆናቸው የመምህሩ ስራ መማር የሚችሉበትን ሁኔታ ማመቻቸት ነው፡፡ ለአብነት ያህል Kroll (1991:8) ካቀረቡዋቸው ጥቂቶቹ፡-

- ተገቢ አላማ ያለው ክንውን ማዘጋጀት፤
- ርዕስን ማስተዋወቅ፤
- ተማሪዎች ለትምህርቱ ተነሳሽነት እንዲኖራቸው ማነቃቂያ ሃሳብ ማቅረብ፤
- ለትምህርቱ ፍላጎት ኖሯቸው እንዲማሩ (እንዲሰሩ)ማነሳሳት፤
- ጤናማ የመምህር-ተማሪና የተማሪ ተማሪ ተራክቦ መፍጠር፤
- መተጋገዝ ዓላማውን ያደረገ የቡድን ምደባ ማድረግ፤
- የማስተማር ጥበብንና ሳይንስን ተክኖ መገኘት፤
- የጥያቄ አጠያየቅና ፤ የተማሪዎችን ምላሽ አቀባበል፤
- የግልና የቡድን ስራዎቸን የመምራትና የማበረታታት፤
- ትክክለኛውን የፅህፈት ትምህርት አቀራረብ መርጦ የመጠቀም ብቃትና ዕውቀት፤ ወዘተ ይገኙባቸዋ፡፡

ለዚህም መምህሩ ስለመማሪያ ክፍሉና በመማሪያ ክፍሉ መከናወን ስለሚገባው ሁኔታ ፅህፈት አዕምሯዊ ተግባር ስለመሆኑና በክፍል ውሥጥም ሊከወን ስለመቻሉ ተገቢው ግንዛቤ ማዳበር እንዳለበት Aggrawal(1995:141) እና Kroll (199:8) ይገልፃሉ፡፡

እነዚህ ምሁራን አክለውም የመምህሩ የማስተማር ችሎታ በተማሪዎች ትምህርት አቀባበል ላይ በከፍተኛ ደረጃ ተፅዕኖ እንደሚያሳድር ጠቁመው የትኛው የአቀራረብ ስልት የተሻለ እንደሆነ ለይቶ መናገር ግን ቀላል እንዳልሆነ ይገልፃሉ፡፡ ስለዚህ የፅህፈት ክሂል ትምህርትን ለማስተማር ወደ ክፍል የሚገባ መምህር ተማሪዎች ውጤታማ እንዲሆኑ በጥሩ የማስተማር ዝግጅትና የፅህፈት ትምህርት አላማዎች ከግብ ሊያደርሱ የሚችሉ ይዘቶችን በተገቢው የማስተማር ስነ-ዘዴ ለማቅረብ ጥረት ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

በሌላ በኩል ተማሪዎች በፅሀፈት አማካኝነት ሃሳባቸውን በተገቢው ሁኔታ ለመግለፅ የሚያስችላቸውን እውቀትና ችሎታ እንዲያዳብሩ ለማድረግ መምህሩ የትምህርቱን አቀራረብ በተማሪዎች ፍላጎትና ችሎታ ላይ የተመሰረተ መሆን እንዳለበትና በአቀራረብ ሂደቱም የሚከተሉትን መርሆዎች መከተል ተገቢ እንደሆነ Atkins et al (1996:11)ይጠቁማሉ፤የፅሀፈት ትምህርት ተማሪዎች በክፍል ውሥጥም ሆነ ከክፍል ውጪ የፅሀፈትን ስራ የሚለማመዱበት መሆን አለበት፡፡ በክፍል ውሥጥ የሚመደበው ክፍለ ጊዜ ለሰዋሰውና በቃላት ትምህርት ብቻ ሳይሆን ተማሪዎች የፅሀፈት ስራዎችን በመለማመድ የፅሀፈት ችሎታን ማዳበር አለባቸው፤በክፍል ውስጥ የሚቀርቡ የፅሀፈት ትምህርት ክንውኖች (ተግባራት)ሳቢና ለፅሀፈት የሚያነቃቁ፣ዓላማ ያላቸው፣የተማሪዎችን ችሎታና ፍላጎት ያገናዘቡ፣ተማሪዎች ሐሳባቸውን በቀላሉ ለመግለፅ የሚያስችሉ፣ለውይይትና በግል፣ በጥንድ፣በቡድንና በህብረት ለመስራት ተስማሚ የሆኑ፣ግልፅ መመሪያዎች ያላቸውና ተማሪዎች እንዲያቅዱ፣እንዲያረቁ፣ እንዲከልሱና እንዲገመግሙ የሚያበረታቱ፣ ወዘተ…መሆን ይጠበቅባቸዋል፤የዕለቱ ትምህርት ርዕስ፣ዓላማ ማስተዋወቅ፣ተማሪዎች እንዲፅፉ ከመነገራቸው በፊት ተማሪዎችን ማነቃቃት ያስፈልጋል፡፡ተማሪዎች በግል፣ በጥንድ፣በቡድንና በህብረት እንዲሰሩ ከተፈለገ በቅድሚያ ግልፅ መመሪያ ሊሰጣቸው ይገባል፤የፅሀፈትን ልምምድ ሲያደርጉ (ተግባራትን ሲያከናውኑ) መከታተል፣ጠቃሚና ገንቢ ምጋቤ-ምላሽ መስጠት፤ ለምሳሌ የተሻለ ሙከራ ያደረጉትን ተማሪዎች በመለየት ድጋፍ መስጠት ማድነቅና ማብራራት፣ፅሁፋቸውን ማረም ፣አስተያየት መስጠት ወዘተ ተማሪዎች መፃፍ የሚፈልጉባቸው ሃሳቦች በመቀበል በተቻለ መጠን ግልፅና ትክክል በሆነ መንገድ ሃሳባቸውን እንዲገልፁ ማበረታታት፣ተማሪዎች ሃሳባቸውን በፅሁፍ የመግለፅ ችሎታቸውን ከተፈለገው ደረጃ ላይ ከደረሰ ፣ ተማሪዎችን ሊፈቱት የሚችሉ አዝናኝ ልቅ ያልሆነ ውሥን ተግባራትን ማቅረብና ተማሪዎች እርስ በርሳቸው እንዲደጋገፉ፣ የፃፉትን ተቀያይረው እንዲያነቡና አስተያየት እንዲሰጣጡ ማበረታታት የሚችሉት ናቸው፡፡

በተጨማሪ የፅሀፈት ትምህርት ተማሪዎች በክፍል ውስጥም ሆነ ከክፍል ውጪ የፅሀፈት ስራ የሚለማዱበት መሆን አለበት፡፡ በክፍል ውስጥ የሚመደበው ክፍለ ጊዜ ለሰዋሰውና ለቃላት ትምህርት ብቻ ሳይሆን ተማሪዎች የፅሀፈት ስራዎችን በመለማመድ የፅሀፈት ችሎታቸውን ማዳበር እንዳለባቸው Atkins et al 1996:11) ይጠቁማል፡፡

Murray (1982) እና Byrne (1988) እንደሚገልፁት ደግሞ፣በፅህፈት ትምህርት መማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ የሚኖር የመምህር ኃላፊነቶች በአራት ይከፍሉቸዋል፡፡ ከዚህ ቀጥሎ እያንዳንዳቸውን እናያለን፤

*2.5.7.2 ጥሩ የመማር ድባብን መፍጠር*

በፅህፈት ትምህርት ወቅት ተማሪዎች የፅህፈትን ስራ በተገቢው መንገድ መስራት እንዲችሉ፣ ምቹና ቀልጣፋና የመማር ዐውድ መፍጠር አስፈላጊ ነው፡፡ ተማሪዎች የተዘጋጀ ስነልቦናና የተመቻቸ አካባቢያዊ ሁኔታ ያስፈልጋቸዋልና፡፡ ስለዚህ መምህሩ ለተፃፈው ፅሁፎችንና ለጽሁፍ ቋንቋም እንዲጋለጡ በማድረግ የጽሁፍ ቋንቋ እንደሚያግባባና የመግባቢያ ዘዴ እንደሆነ ለማሳወቅ ጥሩ የመማር ድባብን መፍጠር አለበት፡፡

*2.5.7.2.3 በማፃፍ ፅሁፈትን ማለማመድ*

ቀደም ብሎ በተፈጠረው ጥሩ የመማር ድባብ በዚህ ክፍል ለተማሪዎች ጥሩ የመስራት እድልን ይፈጥርላቸዋል፡፡ መምህር የተማሪዎቹን ችሎታና ፍላጎት እየተከታተለ በክፍለ ጊዜውና በቀኑ የሚፅፉትን በጊዜና በመጠን ገድቦ በመስጠት ተማሪዎች ባለማቋረጥ የፅህፈት ልምምድ እንዲያደርጉ በየደረጃው የሚሰሩትን ስራ እቅድ እያስቀመጠ መሄድ አለበት፡፡

*2.5.7.4 በፅህፈት ስራ ላይ ተገቢውን ማስተካከያ መስጠት*

ማንኛውም ተማሪ አንድን አዲስ ቋንቋ ወይም ክሂል በሚማርበት ጊዜ ስህተት እንደሚፈፅም አስቀድሞ ማወቅ አለበት፡፡ ተማሪዎች በፅህፈት ልምምድ ጊዜ ለሚፈጥሩት ስህተትም ተፈጥሮአዊና ሊከሰት የሚችል መሆኑን ተረድቶ ማበረታታትና ተገቢውን ምጋቤ ምላሽ (feed back) መስጠት ይገባል፡፡ስህተታቸውን ሲያርም ለፅህፈት ስራቸው የሚሰጠው ነጥብና አስተያየት የተማሪውን ስሜት የማይነካ እንዲሆን መጠንቀቅ አለበት፡፡

ከዚህ በተጨማሪ መምህሩ የተማሪዎችን ፅህፈት በሚያርምበት ጊዜ ዋና ዋና የተማሪ ስህተቶች ምን ምን እንደሆኑ መለየት እና መፍትሄ መፈለግ አለበት፡፡ የተማሪዎች ስህተቶች ፣ ሃሳብን የማደራጀት ችግር፣ የአንቀጽ ግጥምጥምነት ችግር፣ የሰዋሰዋዊ ስህተት ችግር፣ ወዘተ ሊሆን ይችላሉ፡፡ እነዚህን ችግሮች ካየም፣ መፍትሄ ለመጠቆም እንዲያመቸው ቅድሚያ የሚሰጣቸውን መለየት ይጠበቅበታል፡፡ ቀጥሎም በያዘው ቅደም ተከተል መሰረት ትምህርት ይሰጣል፡፡ እርስ በርስ የመማር ልምድ እንዲያጎለብቱም ይመክራል፡፡

## 2.6 የጥሩ ፅህፈት መመዘኛ መስፈርቶች

የመፃፍ ክሒል በባህሪው ዘርፈ ብዙ ነው፡፡ ይህም ሲባል በውስጡ የቃላት አመራረጥ ፣ የዓረፍተ-ነገር አመሰራረት ፣የአንቀፅ አወቃቀር፣ የስርአተ ነጥብ አጠቃቀም የመሳሰሉትን ለመፃፍ ክሂል የሚያስፈልጉ ነጥቦች አካቶ የሚይዝ የክሂል ዘርፍ ነው ለማለት ነው፡፡ ይህን ሀሳብ መነሻ በማድረግ አንድ ፅሁፍ ከሌላው የተሻለ ነው ወይም ጥሩ ፅሁፍ ነው ብሎ ለመለየት የምሁራን መስፈርቶችን መጠቀም ተገቢ እንደሆነ ይስማማሉ፡፡ ለአብነት ያህል ዳዊት (2009 ዓ.ም እና 2010) Nik et al (2010) ጥሩ የመፃፍ ባህሪያት መስፈርቶች ካለው ከዘረዘራቸው ውስጥ ዋና ዋናዎችን እንደሚከተለው በዝርዝር ለማስቀመጥ ተሞክሯል፡፡

### *2.6.1 በቂ ሐሳብ/ይዘት*

በአንድ ጥሩ በሚባል ፅሑፍ ውስጥ በቂ ሀሳብ ማፍለቅ እያንዳንዱ አንቀፅ ሀይለ ቃል መያዝና ይህን ሀይለ ቃል በበቂ መዘርዝር ዓረፍተ ነገሮች በማብራራት ማቅረብ ተገቢ ነው፡፡ከዚህም በተጨማሪ ፅሁፉ አላማውን ያገናዘበ በማስረጃዎች የተደገፈ ግልፅና ፣ማራኪ መሆን ይገባዋል፡፡ይህ እንዲሆንና ስለሚፃፈው ነገር በጥልቀትና በዝርዝር ለማቅረብ የተፈለገውን አለማስተላለፍና ምን አይነት ቋንቋን መጠቀም እንደሚገባ ለመወሠን በቅድሚያ ይዘቱን መረዳትና በቂ የሆነ ሀሳብ ሊኖር ይገባል፡፡

### *2.6.2 የቋንቋ አወቃቅር*

የቋንቋ አጠቃቀም በዋናነት ከተገቢ የሰዋስው አጠቃቀምና አገባብ አንፃር ቢታይ የሚቀል ነው፡፡ ይህም ሲባል በፅሑፍ ሀሳብን ለአንባቢያን ለማስተላለፍ ትክክለኛውን የሰዋሰው ስርዓት መከተልን ያመለክታል፡፡ ይህንንም ባየ /1987 ኢ.ም/ የአንድ ቋንቋ ስርዓት ከድምፅ አሰካክ እስከ ሃረግ አመሰራረት ድረስ የሚያሳይ ሳይንስን ሰዋሰው እንለዋለን በማለት ይገለፃል፡፡ በመሆኑም በመፃፍ ተግባር ላይ ተማሪዎች የሚጠቀሙት ቃል፣ ሀረግና አረፍተ ነገሮች /በቁጥር፣ በጾታ፣ በመደብና በጊዜ/ የተስተካከለና ከሰዋሰው ስርአቶች የፀዳና አንባቢን የማያደናቅፍ መሆን አለበት፡፡

### *2.6.3 የቃላት አጠቃቀም*

ለፅሑፍ ቋንቋ የምንጠቀመው መደበኛ የሆኑ ቃላትንና በንግግር ወቅት የምንጠቀማቸውን ቃላት የተለዩ መሆን አለባቸው፡፡ ይህ ማለት በንግግር ወቅት የምንጠቀማቸውን ቃላት በመፃፍ ጊዜ አንጠቃቅም ለማለት ሳይሆን በፅሁፍ ወስን የቃላት አጠቃቀም ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጠው በድምፅ ቅላፄ፣ በአካል እንቅስቃሴና በፊት ገጽታ ስለማይታገዝ ፀሀፊው

ሃሳቡን በትክክል ለማስተላለፍ በሁሉም ህብረተሰብ የሚታወቁና መደበኛ የሆነ ቃላትን ቢጠቀም የተሻለ ነው ለማለት ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪም ከኢ- መደበኛ የቃላት አጠቃቀም ከሃራም /ፀያፍ ቃላት ፣የአራዳ ቃላት፣ የተሰለቹ ቃላት፣የዚህን ቃላትና ከቃላት ድረታ የፀዳና የመሳሰሉትን ችግሮች ማስወገድ የጥሩ ፅሑፍ ሌላኛው መግለጫ ባህሪው ነው (ዳዊት 2009 ኣ.ም/፡፡

### *2.6.4 ስርአተ-ፅህፈት*

ስርአተ-ፅህፈት ሲባል በውስጡ ከፅሑፍ አጠቃላይ ገፅታ ጀምሮ ከሆህያት መጠንና ቅርፅ ፣ ከመስመር አጠባበቅ የቀኝን ግራ ህዳግ አጠባበቅ እና ስርአተ ነጥብ አጠቃቀም ሁሉ አጠቃሎ የያዘ ሲሆን አጠቃላይ የቋንቋውን የአፃፃፍ ቅርፅ የሚያካትት ነው (ዳዊት 2008ኣ.ም)

### *2.6.5 የሀሳብ አደረጃጀት*

አንድ ጥሩ ድርሰት መግቢያ ሃተታና መደምደሚያ አሟልቶ መገኘት አለበት፡፡ ከአንቀጽ አንቀጽ የተዋቀሩ ዐረፍተ-ነገሮች ተያያዥነትና ተለጣጣቂነት ባለፈ ሁኔታ ዋናውንና ንዑሳን ሀሳቦች ተጠየቃዊ በሆነ መንገድ ተደራጅተው ከሃሳብ ድግግሞሽ መጥራት በፀዳ መልኩ መቅረብ መቻል አለባቸው ፡፡እንደአለማየሁ /1999 ኣ.ም /አገላለፅ ሃሳብን ማደራጀት ሲባል አንድ ፀሃፊ ለመፃፍ ሲነሳ ምክንያት እንዳይልና ሁሉ በፅሑፍ ውስጥ ያሉ ሃሳቦችም ምክንያታዊ አደረጃጀቶች ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ይህ ማለት አንድ ፀሀፊ የሚያነሳቸው ሃሳቦች በአሰተማማኝ ምክንያት ተደግፈው ተጠየቃዊ አደረጃጀትን ተከትለው መቅረብ አለባቸው ለማለት ነው፡፡

## 2.7 የመማር ብለሃት

ብልሃት ማንኛውም ጉዳይ የማከናወን ፣ የመማር ስልት ወይም ክህሎት ነው ፡፡ ወደ ሚጠበቀው ግብ ለማድረስ የሚያገለግል መንገድ ወይም ዘዴ ነው ፡፡ የብልሃትን ምንነት በተመለከተ ምሁራን ከሰጧቸው ብያኔዎች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል ፡፡

Brown (1994,104) ብልሃት አንድን ስራ ለመስራት ወይም አንድን ችግር ለመፍታት የሚያስችል የአማራጭ መንገድ ፣ አንድ ድምዳሜ ላይ ለመድረስ የሚያግዝ ተመራጭ ስልታዊ ተግባር ፣ እንዲሁም አንድን ለመገንዘብ የመረዳት ቅድመ ተግባር አቅድ ነው ፡፡

O,maly and Chamot (1990,20) እንደሚገልፁት ደግሞ ብልሃት በእያንዳንዱ ግለሠብ አዕምሮ ውስጥ የሚገኝ የተለያየ የአሰራር ፀባይ ወይም ባህሪ ነው ፡፡ በተመሳሳይ መልኩ Wharton (2000,204) እና Oxford (1989 , 235) ብልሃትን ሲገለፁ " በተማሪዎች የሚተገበርና መልመድን ፣ ዕውቀት ማጠራቀምን ሀሳብን አስተውሶ መጠቀምን የሚያፋጥን የአሰራር ባህሪ ተግባራዊ ደረጃ ወይም አካሄዳዊ ቴክኒክ ነው ።

### 2.7.1 የብልሃት አከፋፈል

በተለያየ ወቅት ተመራማሪዎች ልዩ ልዩ ደረጃ ላይ ባሉ ተማሪዎችና ከመማሪያ ክፍል ውጭ ሰዎች በራሳቸው ፍላጎት ሲማሩ በሚያሳዩት የመማር ክንዋኔ ላይ ምርምር በማድረግ ልዩ ልዩ ዓይነት የመማር ብልሀቶች እንደተገኙ ይገልፃሉ፡፡ E llis (1994,530) Tarone ( 1980,419) ን ጠቅሰው እንደገለፁት ሦስት አይነት አጠቃላይ ብልሃቶች እንዳሉ ያስረዳሉ ፡፡ እነዚህም ብልሀቶች እንደ ሚከተሉት ቀርበዋል ፡፡

***ሀ. ተግባቦታዊ ብልሀት*** :- ይህ ብልሀት በመግባባት ሂደት ጊዜ የሚከሰቱ ችግሮችን ለመቋቋም የሚያግዝ ነው ፡፡

***ለ. አፍልቆታዊ ብልሀት*** :- ይህ ብልሀት ተቀባይነት አፍላቂ ክሂሎችን ለመልመድና ለመገልገል የሚያገለግል ነው ፡፡

***ሐ. የመማር ብልሀት*** :- ይህ ብልሀት ደግሞ የቋንቋ ስ ነ ልሣናዊና ማህበራዊ ስነ ልሳናዊ ብቃትን በማሣደግ የቋንቋ ዕውቀትን ለማስፋት የሚያግዝ ነው፡፡

በሌላ በኩል O'mally እና Chamot( 1990:137-9) አሜሪካ ውስጥ ባሉ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች በሚማሩ ተማሪዎች ላይ ጥናት በማድረግ ተማሪዎች የሚገለገሉባቸው የተለያዩ የብልሃት አይነቶች እንዳሉ ገልፀዋል::እነሱም የሚከተሉት ናቸው::

1 ማደራጀት:በዚህ ብልሃት ተማሪዎች ወደፊት የሚሠሯቸውን ዋና ዋና ሃሣቦችናይዘቶች ልዩ ልዩ የመረጃ ምንጮችን በማሠስ ቅድመ ዝግጅት የማድረግ ስራ የሚያከናውኑበት ነው፡፡

2 ቀጥተኛ ትኩረት መስጠት፡-አላስፈላጊና ትኩረትን ከሚበታትኑ ነገሮች አዕምሮን ነፃ በማድረግ ትምህርትን በቀጥታ የመከታተል ብልሃት ነው፡፡

3 ራስን መምራት፡-ተማሪዎች በራሳቸው አካሄድ በቋንቋ ለመፃፍ የሚያግዙ ሁኔታዎችንና አጋጣሚዎችን የሚያመቻቹበት ወይምአጋጣሚዎቹ በትክክል መፈጠራቸውን የሚያረጋግጡበት ብልሃት ነው፡፡

4 ማስታወሻ መያዝ፡-በትምህርቱ ሂደት ወቅት ዋና ዋና ሃሣቦችን ወይም ዝርዝር ጉዳዮችን አስፋ

ፍቶ ወይምአሳጥሮናጨምቆ በፅሁፍ መልክ በማስታወሻ ደብተር በመያዝ የትምህርቱን ተግባራዊነትና ውጤታማነት ለማገዝ የሚያስችል ብልሃት ነው፡፡

5 ማጠቃለል፡-በትምህርት ሂደት በማዳመጥ ወይም በማንበብ የተገኘውን ዕውቀት ወይም ፅንሰ ሃሣብ በፅሁፍ መልክ በማሳጠር ጭምቅ ሃሳብ የማዘጋጀት የቋንቋ ስነ-ልሳናዊና ማህበራዊ ስነ-ልሳን ብቃትን በማሳደግ የቋንቋ ዕውቀትን ለማስፋፋት የሚያግዝ ነው ፡፡

## 2.8.1 የመማር ብልሀት

የመማር ብልሀት ተማሪዎች በትምህርት ሂደታቸው ትምህርት ነክ ስራዎችን ለመስራት የሚገለገሉበት ክንዋኔ ፣ ልምድ ወይም ስልት ሲሆን ፣ በትምህርት ያገኟቸውን አዳዲስ ፅንሰ ሀሳቦች ወደ አጭር ወይም የረጅም ጊዜ ትውስታ ለማስገባትና አስፈላጊ በሆኑ ጊዜ ለመጠቀም የሚያስችላቸው ልዩ ልዩ መንገድ ነው።ብልሀት ተማሪዎች የሚያካሂዱትን ትምህርት በብዙ አቅጣጫ በማየት በራሳቸው ምርጫና በሚቀላቸው መንገድ እንዲማሩ የሚያግዛቸው፣ማንኛውንም ትምህርታዊ ክንውንን በራሳቸው ሀይል እየሰሩ እንዲማሩ እገዛ የሚያደርግ ነው ፡፡

## 2.8.2 ድርሰት የመፃፍ ብልሀት

የመፃፍ ተግባር የሚከናወንበትን አጠቃላይ ሁኔታ የተግባር አካባቢ ፣ የፀሀፊው የረጅም ጊዜ የመረጃ ክምችትና የመፃፍ ሂደት በማለት Lindolf ( 1985,155) እና Brown (1985,12) በሶስት ይከፍሉታል ፡፡የተግባር አካባቢ የሚሉት በሞዴላቸው መሠረት ተማሪዎች እንዲፅፉ የሚሰጣቸው ትዕዛዝ ፣ ርዕስ ጉዳይ ፣ አንባቢ ፣ ለመፃፍ የሚያነሳሳቸው ሁኔታና የተፃፈው ፅሁፍ ናቸው ፡፡

የፀሀፊው የረጅም ጊዜ የመረጃ ክምችት ደግሞ ፀሀፊው ስለሚፅፉበት ርዕስ፣ ስለአንባቢውና ስለመፃፍ ሂደት ያለው ዕውቀት ነው ፡፡ የመፃፍ ሂደት ግን ማቀድን ፣ ማደራጀትን ፣ ዓላማ መወሰንን ፣ መከለስን ፣ ማንበብንና ማረምን ሁሉ ያካትታል ፡፡

ድርሰት በመፃፍ ሂደት ውስጥ ተመልሶ ማየት ወይም ወደ ኋላ የመመለስ ሁኔታ ሊኖር ይችላል ፡፡ ፀሀፊዎች ከአንድ ሃሳብ ተነስተው ለመግለፅ የፈለጉትን ነገር በፅሁፍ ለማስተላለፍ ሲሉ መፃፍ ይጀምራሉ ፡፡ ነገር ግን በመፃፍ ሂደት ውስጥ እያሉ ቆም ይላሉ፡ ፡ ቆም የሚሉት ደግሞ ሆን ብለው ወይም ተገደው ሲሆን ይችላሉ።የመፃፍ ብልሃት እንደየፀሀፊው የሚያሳይ ቢሆንም በመፃፍ ሂደት ግን በሁሉም አዕምሮ ውስጥ የሚከናወን

ሀሳብ የማመንጨት መረጃ የመምረጥና የማቀናጀት ፣ የማርቀቅ ፣ የመከለስና የማረም ሂደት መሆኑን ምሁራን ይስማማሉ ፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥም ለማለፍ መጠየቅ፣መመለስ፣ ፍቺ መስጠት፣ቃል ወይም ሐረግ መምረጥ፣መተካት፣ወዘተ ይኖራል፡፡Wenden(1991) ድርሰት በመፃፍ ሂደት ወደ አዕምሮ ከሚመጡ ሀሳቦች በጥንቃቄ መምረጥ፣መላ መምታት፣ ማወዳደር፣ማብራራት፣ አዲሱን መረጃ ቀድሞ ከአዕምሮ ከነበረ መረጃ ጋር ማዋሀድ ወዘተ እና በመጨረሻም የተለያዩ መረጃዎችን በአንድነት በመቀናጀት መፃፍ የመፃፍ ብልሃት መሆኑን ይገልፃሉ፡፡

አያይዘዉም ለፀሀፊው ወይም ለተማሪው መስጠት ስለሚገባው የመፃፍ ነፃነትና ስለተግባቦት ማሰብ በመፃፍ ብልሃት ውስጥ እንደሚካተቱ ያስረዳሉ፡፡Golub(1986)በበኩላቸው ሃሳብን ጨምቆ ማውጣት ፣በቅደም ተከተል ማስቀመጥ፣በአይነት መመደብ፣ማደራጀት፣መተንበይ፣ መጠየቅ፣ማረጋገጥ፡ የተለያዩ ሃሣቦችን በአንድነት ማቀናጀትና መገምገም ሁሉ የማሰብ ክሂል በሚሉት በመፃፍ ብልሃት ስር እንደሚካተቱ ይገልፃሉ፡፡

የመፃፍ ብልሃት ተማሪው ሃሣቡን በፅሁፍ ለመግለፅ ለአላማው መገኘት በንቁም ሆነ ኢንቁ(conscious and unconscious) መንገድ የሚጠቀምበት ሂደት ነው፡፡በታላሚዉ ክሂል ለመጠቀም ወይም ለመስራት ጥረት የሚያደርግበት ዘዴ መሆኑን Richards and Rodgers(1986) እና Richards,John and Weber(1985) ያስረዳሉ፡፡

Laib ( 1991 ) የመፃፍ ብልሀት በተለያዩ ክፍሎች ይመደባሉ ፡፡ የመጀመሪያው የሚፃፍበትን ሀሳብ የማፍለቅ ደረጃ ሲሆን ፣ በዚህ ብዕር መተወር ( theorizing ) ገጠመኝ ምልከታና በምክንያት ማደራጀት ይጠቀሳሉ ፡፡ ሁለተኛው የተገኘውን መረጃ ማደራጀት ነው ፡፡ በዚህም መዋቅር / structure / ቅርፅ / form ) ቅደም ተከተል / sequence /ይገኛሉ ፡፡ ሦስተኛው በቃላትና በዓ.ነገር አወቃቀር ተጠቅሞ ሀሳብን ማስተላለፍ ወይም መግለፅ ነው ፡፡ የመጨረሻ ክንውን ሲሆን ፣ ይህም ተጠናቆ የሚቀርበው ፅሁፍ ነው ፡፡

በአጠቃላይ ከምሁራኑ ሀሣብ መረዳት የሚቻለው የመፃፍ ብልሃት በፀሀፊው ወይም በተማሪው አዕምሮ ውስጥ ከሚመላለሰው ሀሣብ መረጃ መምረጥና ማቀናጀት፣ያንንም ማደራጀት የመጀመሪያውን ረቂቅ መፃፍ፣መከለስና ማረም ከዚያም የመጨረሻውን ፅሁፍ እስከ ማጠናቀቅ ድረስ ያለውን ሂደት መሆኑን ነው፡፡

2.9 የተዛማጅ ፅሁፎች ቅኝት

አጥኝው ባደረገው የንባብ አሰሳ የሰለሞን ዮሀንስ ጥናታዊ ፅሁፍ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ፅሁፎችን በማጣቀስ የሚከተሉትን ተዛማጅ ጥናቶች ለመቃኘት ሞክሯል፡፡ ፡፡

ሰይድ ይመር (1993) በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በቋንቋዎች ጥናት ተቋም አማርኛ በማስተማር ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ “ በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሀፍ የቀረቡትን የፅህፈት ትምህርት ይዘቶች ክንውኖች የማስተማሪያ ስነ-ዘዴ ትግበራ “ በሚል ርእስ ጥናት አካሂዷል ፡፡ የጥናቱ አላማ የፅሁፈትን ክሂል ለማዳበር የተመረጡትን ይዘቶች ለማስተማር መምህራን የሚጠቀሟቸውን የማስተማር ስነ-ዘዴዎች አተገባበር ምን እንደሚመስል መገምገምና በተማሪዎች ችሎታ ላይ ያለውን አንድምታ መግለፅ ነው ፡፡ በጥናቱ የተገኘው ውጤት የሚያመለክተው ፅህፈትን በመማር ማስተማር ሂደት የሚቀርቡት ይዘቶችና መልመጃዎች እንዲሁም ክሂሉን ለማዳበር ስራ ላይ የሚውሉት ስነዘዴዎች ትግበራ ፅህፈትን የማያለማምዱና ለክሂሉ መዳበር አስተዋፅኦ የሌላቸው መሆናቸውን ነው ፡፡ ይህንንም ችግር ለማቃለል የሰጠው የመፍትሄ ሀሳብ ልማዳዊውን የማስተማር ዘዴ ለመለወጥ ትኩረት መስጠትና የመማር ማስተማሩን ሂደት ከግብ ለማድረስ ለቅድመ መደበኛ መምህርነት ስልጠናና ለድህረ መምህርነት ደግሞ በስራ ላይ ማሻሻያ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን ነው ፡፡

ተመስገን ፈቀደ (2001) በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በቋንቋዎች ጥናት ተቋም አማርኛን በማስተማር ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ"በፅህፈት ክሂል ማስተማሪያ ዘዴና የተማሪዎች ድርሰት የመፃፍ ብልሃት ተዛምዶ"በሚል ርዕስ ጥናት አካሂዷል፡፡የጥናቱ አለማ በፅህፈት ክሂል ማስተማሪያ ዘዴና በተማሪዎች ድርሰት የመፃፍ ብልሃት መካከል ያለውን ዝምድና መመርመር ነው፡፡የጥናቱ ውጤትም በመምህሩ የማስተማር ዘዴና በተማሪዎቹ ድርሰት የመፃፍ ብልሃት መካከል ዝምድና አለመኖሩን ያመላከተ ሲሆን፣ለዚህም እንደ ምክንያትነት የጠቀሰው በፅህፈት ክሂል መማር ማስተማር ሂደት መምህራን እነሱ በሚፈልጉት የድርሰት አፃፃፍ ህጎች(መርሆዎች) ላይ በመሆኑ ተማሪዎችም እነዚህን ህጎችና መርሆዎች ተከትለው እንዲፅፉ ስለሚገደዱ የመፃፍ ፍላጎታቸውንና ብልሃታቸውን ባለመጠበቃቸው መሆኑን በጥናቱ አመላክቷል፡፡ለደረሰበት ውጤት እንደ መፍትሄ የጠቀሰው መምህራን የድርሰት ደንቦችን ወይም መርሆዎችን ለማሣወቅ ከሚጥሩ ይልቅ የተማሪዎችን የየግል የአፃፃፍ ብልሃት ለመጠበቅ ትኩረት ቢያደርጉ፣መልካም እንደሆነ ጠቅሷል፡፡

አስቴር ሳሙኤል (1998) በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በቋንቋዎች ጥናት አማርኛን በማስተማር ለ M.A ዲግሪ ማሟያ ” የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የፅህፈት ክሂል የማስተማሪያ ዘዴ ፍተሻ“ በሚል ርዕስ ጥናት አቅርባላች፡፡ የጥናቱ ዓላማ መምህራን የፅህፈት ክሂል ሲያስተምሩ የሚጠቀሙበትን የፅህፈት ማስተማሪያ ዘዴ ከፅህፈት

ማስተማሪያ ዘዴዎች አኳያ መፈተሸ ነው ፡፡ በጥናቱ የደረሰችበት ውጤት በጥናቱ የታቀፉት መምህራን የተማሪዎችን የመማር ሁኔታ አመቻችቶ ለመጠቀም ስለፅህፈት ትምህርት ማስተማሪያ ዘዴዎች አጠቃቅም ያላቸውን ግንዛቤ ዝቅተኛ መሆኑን አመልክታለች ፡፡

አስቴር ሳሙኤል ለደረሰችበት የጥናት ውጤት መፍትሄው መምህራን የተለያዩ የፅህፈት ማስተማሪያ ዘዴዎችን በማወቅ እንደሁኔታው ተገቢነታቸው እየፈተሸ የባህሪይ ለውጥ ሊያስከትሉ የሚችሉ የማስተማሪያ ዘዴዎችን እያቀናጁ ቢጠቀሙ፣ በመምህርነት ሙያ ለሚሰለጥኑ ዕጩ የቋንቋ መምህራን በት/ቤት ቆይታቸው ክሂሎችን ስለማስተማር ዘዴ ኮርሶች ተዘጋጅተው በቂ ስልጠና የሚሰጥበት ሁኔታ ቢመቻች የሚል ነው ፡፡

ሰለሞን ዮህንስ ( 1991 ) አ.አ ዩኒቨርስቲ በቋንቋዎች ጥናት ተቋም አማርኛን በማስተር ለማስተርስ ድግሪ ማሟያ “ የተማሪዎች የአማርኛ ድርሰት የመፃፍ ስትራቴጅና የመምህራን የማስተማር ዘዴ ተጣጥሞሽ፡፡ ” በሚል ርዕስ ጥናት አካሂዷል ፡፡ የጥናቱ አላማ በአዋሳ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ተማሪዎች የአማርኛ ድርሰት በሚፅፉበት ስትራቴጅና መምህራን በሚያስተምሩበት ዘዴ መካከል ያለውን ግንኙነት መፈተሽ ነበር ፡፡ ይህንን በሌላ በኩል የመምህሩን የማስተማር ዘዴ ተመልክቷል ፡፡ በጥናቱ የደረሰበት ነጥብ መምህሩ ተማሪዎች በምን አይነት መንገድ መፃፍ እንደሚፈልጉ አይጠይቁም ፡፡ መምህሩም የድርሰት አፃፃፍ ኮርስን የሚያስተምሩበት ዘዴ እንዲያሟላ የሚፈልጉትን ለማስፈፀም የሚያስችል ተግባር የሚጎላበት አሰራር ሁኖ አግኝቶታል፡፡ መምህሩም ተማሪዎቹ ድርሰት የሚፅፉበትን ርዕስ ከመምረጥ አንስቶ የሚፅፉበትን ቅደም ተከተል እስከመቆጣጠር ያለውን ተግባር እንደሚያከናውኑ አመልክቷል ፡፡ መፍትሄውም በድርሰት ትምህርት ውስጥ ተማሪዎች ጥሩ ድርሰት እንዲፅፉ ከርዕስ መረጣ ጀምሮ አብዛኛውን ተግባር በምርጫቸው እንዲያከናውኑ ቢደረግ ..... ወ.ዘ.ተ የተሻለ መሆኑን ጠቁመዋል ፡፡

## ምዕራፍ ሦስት

### 3. የአጠናን ዘዴ

#### 3.1 የጥናቱ ንድፍ

ይህ ጥናት የሚከተለው ከፊል ሙከራዊ (Quasi-Experimental) የጥናት ንድፍ ሲሆን ጥናቱ በአይነቱ መጠናዊ የምርምር ዘዴ ነው፡፡

በዚህ መሠረት ይህ ጥናት የዕህፈት ክሂል ማስተማሪያ ዘዴ በነፃ ተለዋዋጭነት እንዲሁም የተማሪዎችን ድርሰት የመፃፍ ብልሃት በጥገኛ ተለዋዋጭነት በብዙ ባህሪያቸው ተመሳስለው በነፃ ተለዋዋጩ ብቻ ሊለያዩ የሚችሉ ሁለት ቡድኖችን በመውሰድ ተካሂዷል፡፡ቡድኖቹ ማነፃፀሪያ ወይም የቁጥጥር ቡድን (Controlled Group) ሲሆን ሁለተኛው ቡድን ደግሞ ተጠኚ ቡድን (Experimental Group) ሆኗል፡፡በቅድመ ትምህርት ፈተና (Pre-Test) እና ድህረ ትምህርት (Post-Test) በተደገፈ ሁኔታ ተጠኙ ቡድን በነፃ ተለዋዋጩ ምክንያት የሚታይበትን ለውጥ ለመመርመር ተሞክሯል፡፡በዚሁ መሠረት አጥኚው ሁለቱ ቡድኖች የሚለያዩበትን ባህሪ (ማለትም ነፃ ተለዋዋጭ በተጠኚ ቡድኑ ባህሪ ላይ የሚያመጣውን ተፅዕኖ) በመለካት የተጠኚ ቡድን ባህሪይ ከተለመደው ወይም ከአይነተኛው ባህሪይ  ምን ያህል እንደሆነ የቁጥጥር ቡድኑ ባህሪይ እንደማወዳደሪያ መስፈርት በመውሰድ መደምደሚያ ላይ ደርሷል፡፡

#### 3.2 የተጠኝዎች  ተማሪዎች ናሙና አመራረጥ

ጥናቱ የተካሄደበት ትምህርት ቤት ውስጥ የሚማሩ ጠቅላላ የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች 432 ሲሆኑ በጥናቱ የተሳተፉ ተማሪዎችን ለመምረጥ ከተደለደሉበት ክፍሎች ከሚማሩ የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች መካከል የነሲብ ናሙና ዘዴን (Random sampling method/ በመጠቀም የተመረጡ ናቸዉ ፡፡ በዚህም መሠረት ከየምድብ ክፍሎቹ መካከል 20 በመቶ የሚሆኑት ማለትም 86 ተማሪዎች  ተመርጠዋል፡፡

#### 3.2 1 የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ

ለጥናቱ የተመረጠው በአማራ ክልል ምዕራብ ጎጃም ዞን ቋሪት ወረዳ ውስጥ ሦስት የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚገኙ ሲሆን፣ከእነዚህም ውስጥ አጥኚው የሚያስተምርበት የሚገኘው የገነት አቦ 2ኛና መሰናዶ ትምህርት ቤት በአመቺ የንሞና ዘዴ (convenance sampling)  የተመረጠ ሲሆን፡  ይህም ትምህርት ቤት የተመረጠበት

ምክንያት አጥኝው በመምህርነት እየሰራበት ያለ በመሆኑ በቂ የሆኑ መረጃዎችን ሊያገኝ ስለሚችል ነው ፡፡

### 3.2.2 የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ

ለጥናቱ የተመረጠው የክፍል ደረጃ 11ኛ ክፍል ሲሆን ፣ የጥናቱ ተተኳሪዎችም የ11ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራንና ተማሪዎች ናቸው፡፡ ይህም የክፍል ደረጃ ሊመረጥ የቻለው ሆን ተብሎ በአላማ ተኮር /purposive sampling / ተማሪዎች ዩኒቨርስቲ ለመግባት የሚዘጋጁበት በመሆኑና ከሌሎቹ የክፍል ደረጃ ከሚማሩ ተማሪዎች በተሻለ ሁኔታ መረጃ ሊሰጡ ይችላሉ ተብሎ ስለታሰበ ነው ፡፡

### 3.2.3 የመምህራን ናሙና አመራረጥ

ለጥናቱ በተመረጠው ትምህርት ቤት ውስጥ 11ኛ ክፍልን በማስተማር ላይ የሚገኙት መምህራን ሁለት በመሆናቸው ሁለቱም በጠቅላይ የንሞና ዘዴ በጥናቱ እንዲካተቱ ተደርጓል ፡፡

## 3.3 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

ይህን ጥናት ከዳር ለማድረስ የሚያገለግሉት ሁለት የመረጃ መሠብሰቢያ ዘዴዎች ቃለ መጠይቅ፣ የቅድመ ትምህርትና ድህረ ትምህርት ፈተናዎች ናቸው፡፡

### 3.3.2 ቃለ መጠይቅ

ለጥናቱ መረጃ ለመሰብሰቢያነት ያገለገለው ቃለ መጠይቅ ሲሆን ፣ እነዚህም ቃለ መጠይቆች ለመምህራን በማቅረብ ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎች ተገኝተውበታል ፡፡ በዚሁ መሰረትም መምህራን የጽህፈትን ክሂል እንዴት ባለ ዘዴ እንደሚያስተምሩ፡ በመማር ማስተማሩ ሂደት ያላቸዉን ድረሻ፡ አስተያየትና ግንዛቤ ለመፈተሽ እንዲሁም ተማሪዎች ጽህፈትን (ድርሰትን) ለመለማመድ (ለመጻፍ) የሚያደርጉትን ጥረት ለማወቅ በሚያስችል መልኩ ጥያቄወቹ ተዘዘጋጃተዋል፡፡ የቃለ መጠይቆቹ ጥያቄዎች በአጥኝዉ ተዘጋጅተዉ በአማካሪ ከተገመገሙ በኋላ ተሸሽለዉ ተግባራዊ ሆነዋል፡፡ ምላሾችም በመቅረፀ-ድምፅ ከተቀዱ በኋላ ወደ ጽሁፍ ተመልሰዉ የተገኙት መረጃዎች ተተንትነዋል፡፡

### 3.3 3 ፈተና

የዚህን ጥናት ዉጤት ሊያመለክቱ የሚችሉ መረጃዎች በፈተና ተሰብስበዋል፡፡ ፈተናዉ የተሰጠዉም ሁለት ጊዜ ሲሆን የመጀመሪያዉ የሙከራ ፈተና የተሰጠዉ ትምህርት ከመሰጠቱ በፊት (ቅድመ-ፈተና) ሲሆን፡ ሁለተኛዉ ደግሞ ትምህርቱ ተሰጥቶ ከተጠናቀቀ በኋላ (ድህረ-ፈተና) የተሰጠ ነበር፡፡የቅድመ ፈተናው ዋና አላማ ተማሪዎች ከጥናቱ በፊት የፅህፈት ክሂል የችሎታ ደረጃ ተመጣጣኝ መሆን አለመሆኑን ለመፈተሽ ነው፡፡ሁለተኛው

ድህረ ፈተና ሲሆን ዋና ዓላማውም የሙከራና የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች በተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎች ከተማሩ በሁዋላ የመፃፍ ክሂላቸው መሻሻል አለመሻሻሉን ለማረጋገጥ ነው፡፡

ቅድመና ድህረ ፈተናዎቹ የተለያዩ ጥያቄዎች ሆነው ተመሳሳይ የአጠያየቅ ስልትን የተከተሉ እንዲሆኑ ተደርገዋል፡፡ፈተናዎቹ የተለያዩ እንዲሆኑ የተደረገበት ምክንያት ምናልባትም አንድን ፈተና ሁለት ጊዜ ሲፈተኑ ቀደም ሲል ስለመለሱት መልስ የማስታወስ አቅማቸው ከፍተኛ ሊሆን እንደሚችል በማሰብ ነው፡፡ቅድመ ትምህርት ፈተናው ለቁጥጥር ቡድኑና ለሙከራ ቡድኑ አንድ አይነት ሆኖ በተመሣሣይ አውድ በሁለት መማሪያ ክፍሎች ተሰጥቷል፡፡የቅድመ ፈተና ትምህርቱ አላማ በጥገኛ ተለዋዋጭና በነፃ ተለዋዋጭ ምድቦች ተከፍለው የሚጠኑት ሁለት ቡድኖች ከሂደታዊ የፅህፈት ክሂል ማስተማሪያ ዘዴው ትግበራ በፊት በሚቀርብላቸው ፈተና አማካኝነት የሚገኙበት ደረጃ ለመለየት የሚያገለግል ሆኗል፡፡

አጥኚው ቅድመና ድህረ የመፃፍ ፈተናዎችን ለማዘጋጀት መማሪያ መፅሀፉ ውስጥ የቀረቡትን የመፃፍ ተግባራት በመፈተሽ ጠቋሚ የመፃፍ ጥያቄ (Guided writing) ለተማሪዎቹ ስለአንድ ርዕሰ ጉዳይ ዝርዝር መረጃ ቀርቦላቸው ፣ከመረጃዎቹ በመነሳት አደራጅተው እንዲፅፉ የሚያስችል ነው፡፡

በሌላ በኩል የነፃ መፃፍ (free writing) ጥያቄ፣ዋና ዓላማው ተማሪዎቹ ስለአንድ ርዕሰ ጉዳይ ተጠይቀው በራሳቸው አፍልቀው እና አደራጅተው ድርሰት እንዲፅፉ ማስቻል ነው፡፡ ከዚህም በመነሳት በአካባቢያቸው ስለሚያውቁት ነገር፣ ድርሰት እንዲፅፉ ተደርጓል፡፡ ከተማሪዎቹ የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ጋር አብሮ መሄድ የሚችሉ ገላጭ ድርሰት መፃፍ የሚያስችሉ ሁለት ነፃ የመፃፍ ጥያቄዎች እንዲሁም ሁለት ጠቋሚ ጥያቄዎች እንዲዘጋጁ ተደርጓል፡፡የተዘጋጁት ጥያቄዎችን ገላጭ እና አመዛዛኝ በሚል በሁለት ምድብ እንዲከፈሉ ከተደረገ በሁዋላ በተራ የዕጣ ናሙና ስልት ከሁለቱ ምድቦች አንድ-አንድ ዕጣ እንዲነሳ ተደርጓል፡፡የተነሱትም ገላጭና አመዛዛኝ ድርሰት በቅድመ ፈተናው እንዲመረጡ ሲደረግ፣ በተመሣሣይ የቀሩት ድርሰቶች ለድህረ ፈተናው ሊመረጡ ችለዋል፡፡ተተኳሪ የሆኑት ተማሪዎች የተፈተኑትን የቅድመና ድህረ ፈተና በተመረጡ ሶስት መምህራን እንዲታረሙ ተደርጓል፡፡

### 3.3.3.1 የማስተማር ትግበራ

አጥኚው በናሙናነት የተመረጡትን 86 ተማሪዎች በቀላል የእጣ ናሙና ስልት በመምረጥ 43 ተማሪዎችን የቁጥጥር ቡድን፣በተመሣሣይ 43 ተማሪዎችን ደግሞ የሙከራ ቡድን ተጠኚዎች አድርጎ በሁለት መማሪያ ክፍሎች፣ አንድ መምህር ተመርጦ ድርሰት የመፃፍ ክሂል ተግባራት ከመማሪያ መፅሀፉ ውስጥ ለ 12 ክፍለ ጊዜያት በሣምንት ሦስት ቀን፣ በተቃራኒ ፈረቃ ትምህርቱን በቀን ለ 40 ደቂቃ ያህል እንዲማሩ ተደርጓል፡፡

የሙከራ ቡድኑ አባላት ሂደት ተኮር የፅህፈት ክሂል ማስተማሪያ ዘዴን ተከትለው ፅህፈትን እንዲማሩ ሲደረግ የቁጥጥር ቡድኑ አባላት ደግሞ ውጤት ተኮር የፅህፈት ክሂል ማስተማሪያ ዘዴን ተከትለው ፅህፈትን እንዲለማመዱ ተደርጓል፡፡

በዚህ የዋና ጥናት ሂደት የማስተማር ትግበራው ወቅት ይህንንም ተግባር ለማከናወን አጥኚው በዓላማዊ የናሙና አመራረጥ ዘዴ ተተኳሪዎቹን ለማስተማር አንድ መምህር መርጧል፡፡የተመረጠው መምህርም የሙከራ ቡድን ተማሪዎችን የመፃፍ ክሂልን በሂደት ተኮር የፅህፈት ክሂል ማስተማሪያ ዘዴ፣የቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች ደግሞ በተለምዷዊው የማስተማር ዘዴ የመፃፍ ክሂልን እንዲማሩ ተደርጓል፡፡

የቁጥጥር ቡድኑ ውጤታዊ የፅህፈት ክሂል ማስተማሪያ ዘዴን ተከትለው ጥሩ ተፅፈዋል የተባሉትን ሞዴል ፅሁፎች አቅርቦ ሰዋሰዋዊ ህጎችን፣አደረጃጀቶችን፣የአፃፃፍ ብልሃቶችን ወ.ዘ.ተ በማሣየት ተማሪዎቹ እነዚያኑን አስመስለው ድርሰት እንዲፅፉ ተደርጓል፡፡ ተማሪዎቹ የፃፏቸው የፅህፈት ተግባራት በቋንቋው ሰዋሰው ላይ ያተኮሩ ነበሩ፡፡እንዲሁም በመምህሩ አማካኝነት ተመርጦ በተሠጣቸው ርዕስ ትኩረታቸውን በቋንቋው መዋቅር ላይ አድርገው፣ሰዋሰዋዊ ስህተቶቻቸውንም በቋንቋው አጠቃቀም ላይ ጥንቃቄ አድርገው ድርሰት እንዲፅፉ ተደርጓል፡፡በልምምድ ወቅትም ተማሪዎቹ በተሰጧቸው ርዕስ ዙሪያ ሀሳብ አፍልቀው በሚፅፉበት ጊዜ መለኪያው ሰዋሰዋዊ ስህተቶች ያልበዙበት ፅሁፍ መፃፉን መሠረት ያደረገ ነበር፡፡በመጨረሻም መምህሩ የቁጥጥር ቡድኑ የፃፉትን ድርሰት በመሠብሰብ ሰዋሰዋዊ ስህተቶችንና የአፃፃፍ ግድፈቶችን በማረም፣የፅሁፉን ጥሩነትና መጥፎነት ከትክክለኛነት አንፃር መገምገምና ውጤት ለመስጠት ተሞክሯል፡፡

የሙከራ ቡድኑ ደግሞ በሂደታዊ የፅህፈት ክሂል ማስተማሪያ ዘዴ ትምህርቱን የተማሩ ሲሆን፣ተማሪዎቹ በራሳቸው የመማር ፍጥነት እንዲለማማዱ፣ስለሚፅፉት ድርሰት የአፃፃፍ

